መለምቺ

ቁጥር 2 - ሚያዝያ, 2012

ኢትዮጵያ ከ163 ሀገሮች 131ኛ

ሴቶችና ሰብአዊ ልማት በኢትዮጵያ

ሴቶች ብቻ - only Women››

የጾታ እኩልነት ሂሳብ

የተረሳ ጣጣ

በኢንሽዬቲቭ አፍሪካ እየተዘጋጀ በዓመት አራት ጊዜ
የሚቀርብ የጀንደር ኔትዎርክ መጽሔት

ከዝግጅት ክፍሉ

ኢንሸዬቲቭ አፍሪካ እ.ኤ.አ በ2002 የተቋቋመ እና ከመንግስት እውቅና ያለው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አካል ነው። ድርጅቱ ባለፉት 17 ዓመታት በዲሞክራሲ፣ በሰብዓዊ መብት እና በመልካም አስተዳደር እንዲሁም በግጭት አፈታት፣ ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም እና ሴቶችን ማብቃት፣ ህብረተሰብን መገንባት፣ በተጨማሪም በአካባቢ ልማት የወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ ዙሪያ ፕሮግራሞችን ቀርፆ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር በሀገራችን በተመረጡ አካባቢዎች ተንቀሳቅሷል። በመንቀሳቀስ ላይም ይገኛል።

ድርጅቱ በተለይ እ.ኤ.አ. ከ2019 ጀምሮ ከላይ ከተጠቀሱት ፕሮግራሞች በተጨማሪ ስርዓተ ፆታን አካታች በሆኑ አሳታፊ የመማር ማስተማር እና የምዘና ዘዴዎች ላይ ያተኮሩ ተግባሮችን ያከናውናል። በሀገራችን በየጊዜው በሚከናወኑ ህዝበ ውሳኔዎች እና ምርጫዎችን መታዘብ፣ የምርጫ ውይይት ማካሄድ እና የምርጫ አስተያየት መሰብሰብ እና ሪፖርት ማዘጋጀት እንዲሁም አማራጭ አቅራቢዎች ሃሳብ የሚያቀርቡበትን መድረክ ማመቻቸት እና ማወያየትም ድርጅቱ ከሚያከናውናቸው ስራዎች መካከልም ተጠቃሽ ናቸው።

እንደ ኢንሸዬቲቭ አፍሪካ ያሉ በሥርዓተ ጾታ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች በመተባበር በስዊድን ኤምባሲ ድጋፍ አንድ የጋራ የትስስር ቡድን ያቋቋሙ ሲሆን ይህ መጽሔትም የዚህ ትስስር አባላት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት የሚያስተዋውቁበትና የትስስሩም አንድ ውጤት ነው።

የዚህ መጽሔት ዐቢይ ዓላማም ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት መካከል በስርዓተ ፆታ እኩልነት እና መብት ዙሪያ አስተማሪነት እና አዝናኝነት ያላቸውን ፅሁፎች፣ መጣጥፎች እና ካርቱኖች ለህብረተሰቡ በተለይም ሴቶችን መሰረት በማድረግ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስፋት እና የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ ማስቻል ነው።

ለአንባቢያን

መላ ምቹ በነጻ የሚሰራጭ የጀንደር ኔትዎርክ መጽሔት ሲሆን በየሩብ ዓመቱ በድርጅቱ ይዘጋጃል። በዚህ መጽሔት ላይ አስተያየት፣ ጥያቄ፣ ፅሁፍና ካርቱን ካላችሁ በኢሜል info@initiativeafrica.net እና በፖ.ሳ.ቁ 1123 ብትልኩልን ለማስተናገድ ዝግጁ ነን።

ማውጫ

ገጽ

ጩሀ ጩሀ አለኝ ____ 1

ጥንስሱ ____ 2

ኢትዮጵያ ከ163 ሀገሮች 131ኛ ____ 4

<<ሴቶች ብቻ - only Women>> ____ 5

የሞዴስ ነገር ____ 6

ሴቶችን ከውሳኔ ሰጪነት ከማብቃት ____ 7

የጾታ አኩልነት ሂሳብ ____ 8

የጀበና ቡና ____ 9

ባህላዊ የስፌት አቃዎች ____ 10

ሴቶችና ሰብአዊ ልማት በኢትዮጵያ ____ 11

በአለም የኢኮኖሚ ፎረም ላይ ስለሴቶችና ልማት ምን ይሰማል? ____ 12

ጎልማሳ ሊስትሮዎች ____ 13

አኔ አወጽሻለሁ ____ 14

ተስፉና ስጋት - የወጣቷ ህይወት ____ 15

የኩላሊት ነገር ____ 18

የተረሳ ጣጣ ____ 19

ከጽንገተኛ ሞት ይሰውረን ____ 20

ጩህ ጩህ አለኝ

አያሌው አስረስ

መስቀል አደባባይ አጠገብ በሚገኘው አዲስ አበባ ሙዝየም ውስጥ ባለፈው ጊዜ አንድ አውደ ትርዒት ቀርቦ ነበር። አውደ ትርዒቱን ያዘጋጁት ሴታዊቶች ናቸው። ሴታዊት ከኢንሽዬቲቭ አፍሪካ ጋር የሚሠራ የሴቶች ድምጽ በመሆን ስለሴቶች መብት የሚቆምና ሴቶችን በማብቃት ላይ ያተኮረ የሴቶች ስብስብ ነው። < <ምን ለብሳ ነበር? > > በሚል ርእስ የቀረበው ይህ አውደ ርእይ ያተኮረው አለባበስን ተንተርሶ በሴቶች ልጆች ላይ የተፈጸመውን የወሲብ ጥቃት በማሳየት ላይ ነው። እኛ ደግሞ ጾታ እንጂ አለባበስ የመደፈር ምክንያት አይደለም፤ ያ ባይሆን ኑሮማ የአለቀ የተማሪ የደምብ ልብስ (ዩኒፎርም) የለበሰችው መክሊት በምን ምክንያት ትደፈራለች? ብለን እንሞግታለን። ፊት ለፊት አያምጡት እንጂ የእነሱም መሻት ይህን ማስረገጥ ነው።

ጥቃቱ የተፈጸመባቸውን ልጆች በእድሜ ስናይ ደግሞ የሰባት አመቷን አሚናን እና የአስራ ዘጠኝ አመቷን መንበረን እናገኛልን። ጥቃቱ የደረሰባቸው 16 ሴቶች ሲሆኑ ጥቃት አድራሽ ወንዶች ደግሞ 17 ናቸው። ይህ ማለት አንደኛዋ በሁለት ወንዶች ተደፍራለች ማለት ነው።

ጥቃቱን ከፈጸሙት 17 ወንዶች ለሕግ የቀረቡት ሁለት ብቻ ናቸው። በሕግ ቁጥጥር ሥር ገብቶ የነበርው ሶስተኛው አጥቂ ለፖሊስ ጉቦ ሰጥቶ መውጣቱና መልሶም አለመያዙ ተገልጧል። አራተኛው ደግሞ በዋስ ወጥቶ በዚያው ጠፍቷል።

የመደፈር አደጋ ከደረሰባቸው ውስጥ አንዷ ኮከብ የተደፈረችው ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ነው፤ እስረኛ ሆና ተገኝታ አይደለም ሕግ የጠብቀኛል ብላ ገብታ እንጂ። ከታሪኩ የድርጊቱን አፈጻጸም መገመት ይቻላል። ኮከብ ከመኖሪያዋ ብዙም ወደማታውቀው አካባቢ ርቃ ሔዳለች። ልትመለስ ስታስብ ጊዜው መሽቷል። በዚያ የምታውቀው ያሳድረኛል የምትለው ሰው ወይም ዘመድ የላትም። ስለዚህም ፖሊስ ጣቢያ ተጠግታ አድራ በሰላም ወደ አካባቢዋ ለመመለስ ወስና ጣቢያ ትሔዳለች። በቦታው የነበሩት ፖሊሶች በሃሳቧ ተስማምተው ከሴት እስረኞች ጋር እንድታድርና ጠዋት ወደ አገሯ እንድትሔድ ይወስናሉ። ተረኛ ፖሊሱ ግን ወስዶ ከሴት እስረኞች ጋር እንድታድር አላደረገም። ከእርሱ ጋር እንድታድር አድርጎ ደፈራት። ጠዋት ላይ ወስዶ ከሴት እስረኞች ጋር ሲቀላቅላት እስረኞቹ ተቃወሙ። ስለዚህም ወንጀሉ ተጋለጠ። ምን ያደርጋል እሱም ለሕግ አልቀረበም። ጩህ ጩህ ያለኝ ለዚህ ነው።

በአክስትና ባጎት እጅ አድገው ለቁም ነገር የደረሱ ብዙዎች ቢኖሩም የቤዛዊት እጣ ግን ያማል። < <መጣችልህ የፈለግከውን አድርጋት> > ብላ አሳልፋ ለደፋሪው የሰጠቻት ወገኔ ብላ የተጠጋቻት እንደ አንድ የቤት ሠራተኛ አገልጋይዋ አድርጋ ጉልበቷን ስትበዘብዛት የነበረችው አክስቷ ናት።

የሰባት ዓመቷ የአሚና እና የአስራ ስምንት ዓመቷ የአርሴማ ጥቃት ደግሞ ለመናገር እራሱ ይከብዳል። ሰው ከሰውነት ወርዶ ፍጹም እንስሳ ሆኖ በእንስሳነት ባሕሪውና ተግባሩ የተገለጠበት ድርጊት ነው። አርሞ ኮትኩቶ ለቁም ነገር ማድረስ የነበረበት አባት የገዛ ልጁን ሲደፍር በምን ቃል ምሬትንና ጥላቻን መግለጥ ይቻላል? የክርስትናና የእስልምና ወይም የሌላ እምነት ተከታይ ሃይማኖተኛ ሕዝቦች ነን የምንል ሰዎች የሞራል ልዕልናችን ወድየት አለ? ብሎ መጠየቅ ግድ ይሆናል። ይህ አይነቱ ቅሌትና የሞራል ዝቅጠት አያስጮህም?

በመጠቃታቸው የደረሰባቸው ጉዳት ሳያንስ አንዳንዶቹ ለማርገዝና ለመውለድ ተገድደዋል። አክስቷ ለመደፈር የዳረገቻት ቤዛዊት ልጇን ለማየት ምን ያህል ትጠላ እንደነበር የምትናገረው ምርር ባለ ቃል ነው። መከራውንና የመከራውን ማስታወሻ በአንድነት ለመያዝ መገደድ እሷን አታድርገኝ ያሰኛል።

ከአስራ ሰባቱ የወሲብ ጥቃት ፈጻሚዎች አስራ አምስቱ ለሕግ ቀርበው ተገቢውን ቅጣት አላገኙም። ጥፋቱ እንደተራ ጉዳይ ታይቶ ፋይሉ የትም ተጥሎ ይሆናል። ተበዳዮች ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተመላልሰው ነገሩን ለመቀስቀስ ሲነሱ ምን እንደሚጠብቃቸው አይታወቅም። ምናልባት መጠቋቆሚያም እየተደረጉ እየተሸማቀቁ ተጨማሪ ጉዳት ላለማስተናገድ ቢቀርስ ብለው ነገሩን ትተውት ሸሽተው ቤታቸው ገብተው ዘግተውም ይሆናል። መጮህ አሁንም መጮህ የሚያስፈልገው በሕግ አስፈጻሚው ላይ ነው። እነእከሌ ምን ሆኑ የሚሉ ተጨማሪ ጥቃት ፈጻሚዎች እያበዛብን መሆኑ ሊነገረውና ሊሰመርበት ይገባል። ሁሉም ማለት ይቻላል ልጇ ተጎዳች ብሎ ከጎናቸው የሚቆም ሰው ያላቸው አይደሉም። ስለዚህም እጮሃለሁ ጉዳዩን የያዛችሁ ሕግ አስፈጻሚ አካላት እንባቸውን ጥረጉላቸው ብዬ።



ጥንስሱ

ኢንሽዩቲቭ   አፍሪካ

በአውሮፓ ሴት ልጅ ካገባች በኋላ የራሷ ስም ውድቅ ተደርጎ በባሏ ስም መጠራት ትጀምራለች። በእዚህ እኛ እንሻላለን። ማንም ሴት ስለ አገባች ስሟን አትለውጥም። ለሙሽራዋ በባሏ ቤተሰብ የሚወጣላት የዳቦ ስም ቢኖርም በቤተሰቡ ውስጥ ይቀራል እንጂ አደባባይ ወጥቶ አብሯት ያደገውን ስሟን አያሳጣትም። እስከምናውቀው ድረስ በየትኛውም አለም አንድም ሴት ዘጠኝ ወር አርግዛ ዓመት ሁለት ዓመት አጥብታ የምታሳድገውን ልጇን በስሟ ጠርታ አታውቅም። ተጠርቶ ቢገኝ ኅብረተሰቡ መሳቂያ መሳለቂያ አድርጎ አገር ሁሉ ለቅቆ እንዲሰደድ ሊያድርገው ይችላል።

በሰሜኑ ኢትዮጵያ አንድ ሴት ባሏ ከአካባቢው ርቆ በሔደ ጊዜ እንጀራ ጋግራ ወጥ ሠርታ እንድትበላ አይፈቀድም። ለእርሷ የሚፈቀድላት ጥራጥሬው አሸር በአሸሩ ምግብ ነው። ያማረ ከበላች "ሆዳም" ከሚለው ነቀፌታ ጀምሮ ብዙ ጥርጣሬ ሊጫንባት ይችላል። ሌላውን እንተወው ዳቦ የመቁረስ ሥልጣን የላትም።

የሴት አገሯ ባሏ ነው ስለሚባልም በጣም ለብዙ ዘመናት ሴቶች በኢትዮጵያ ከመሬት ውርስ ሲነቀሉ ኖረዋል። በተንቀሳቃሽ ንብረትም ጊዜ ድረሻቸው በጣም በትንሹ የተወሰነ ነበር። ብዙ ጊዜ የንብረት አስተዳደሩን ወንዶች (ወንድሞች ወይም የቅርብ ዘመዶች) እየወሰዱት ባዶ እጃቸውን የሚቀሩበት ጊዜም አለ።

ለልጆቻቸው የቅርብ ጠባቂ፣ ተንከባካቢ፣ አስተማሪና አራሚ እናቶች ቢሆኑም፣ እናቶች አባትም እናትም ሆነው ያሳደጓቸው ብዙ ልጆች ከፍ ላለ ደረጃ የደረሱ ቢሆንም ፣ በአንጻሩ በአባት እጅ አድጎ ሌባ፣ ወሮበላ፣ ዋልጌና በዋል ፈሰስ ብዙ ልጅ ቢኖርም "የሴት ልጅ" ወይም "ሴት ያሳደገው" የሚለው የዘለፋ ቃል በዚህ አገር አጥንት የሚሰብር ደም የሚያፈላ ስድብ ሆኖ ዛሬም ድረስ መዝለቁ መጠቀስ ይኖርበታል።

የወንድን ሰካራምነት የተፈቀደ ተግባር አድርጎ የሚያየው ባህላችን "የሴት ጠጪ የግመል ፈንጪ የለውም" ከሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ጀምሮ ሴቶችን የሚጫኑ በርካታ ምሳሌያዊ አነጋገሮች አጭቆ ይገኛል። "ሴትና አህያ ችግር ይችላል" ከሚለው ሴትን እና አህያን እኩል ከሚያየው ምሳሌ በላይስ የከፋ ነገር ምን መጥቀስ ይቻላል? ሴት ልጅ ተምራ የት ልትደረስ የሚለውም ቢሆን መች ጤነኛ ነው?

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም (UNDP) እ.ኤ.አ. በ2012 ባወጣው አመታዊ ሪፖርት፣ በሴቶች መብት አጠባበቅ ከ188 አገሮች ለኢትዮጵያ የሰጣት 174ኛ ደረጃ መሆኑ አገራችን ምን ያህል ሥር በሰደደ ችግር ውስጥ መሆኗን የሚያሳይ ነው።

ደቡብ ጎንደር ከሚገኘው ከእኛው አውራምባ መንደር በስተቀር አለም በጾታ ጭቆና ፍዳዋን እንደምታይ ነጋሪ አያስፈልግም። በተባበሩት መንግሥታት የአለም ጤና ድርጅት እ.ኤ.አ. በ2004 ባወጣው ሪፖርት እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ 150 ሚሊዮን ሴቶችና 73 ሚሊዮን ወንዶች ባንድ ወይም በሌላ መንገድ ጾታዊ ጥቃት እንደሚደርስባቸው ገልጧል። እነጎሣዬ ባደረጉት ጥናት ደግሞ ከ50% እስከ 67% የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች በእድሜያቸው ቢያንስ አንድ ጊዜ ጾታዊ ጥቃት እንደሚደርስባቸው አመልክተዋል።

ይህ ወደ አደባባይ ሳይወጣ የሚቀረውን አይጨምርም። በምሥራቅ ኢትዮጵያ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አቶ በቀለ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ባደረገው ጥናት 68% በሚሆኑ ሴቶች ላይ ወሲባዊ ጥቃት እንደሚፈጸም አሳውቋል።

በደቡብ አፍሪካ በአንድ የገጠር መንደር እ.ኤ.አ. በ2012 በተደረገ ጥናት ደግሞ በትምህርት ቤት መምህራን ብዙ ጾታዊ ጥቃት ስለሚፈጸሙ ጥቃቱ "ሕጋዊ" እንዲመስልና ዘለቄታ እንዲያገኝ በማድረግ ድርሻ እንዳላቸው፣ ብዙ አጥኚዎች ደግሞ ጥቃት አድራሾች ተማሪዎችን ብቻ አድርገው ስለሚያስረዱ የመምህራኑ ሚና መሸፋፈኑን ዘግቧል።

በአዲስ አበባና በምዕረብ ሸዋ 1401 ተማሪዎች ላይ የተደረገ ጥናት 74% የሚሆኑት ሴት ተማሪዎች ላይ ጾታዊ ማሸማቀቅ እንደሚደርስ ተጠቅሷል። በሀዋሳ ሴት የኮሌጅ ተማሪዎች በሚደርስባቸው ጥቃት ለድብርት መጋለጣቸውም ታውቋል። እነዚህ ሁሉ ምልክቶች እየታወቁ ያሉት ችግሩ አደባባይ የማይወጣ ገመና ሆኖ በሚቆጠርበት አገር መሆኑ ግንዘቤ ማግኘት አለበት።

መርካቶ አካባቢ በሚገኝ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጾታዊ ጥቃት ላይ የተደረገውን ጥናትና መምህራን የሰጡትን አስተያየት ቀረብ ብሎ እንደሚከተለው ማየት አስፈላጊ ይሆናል።

በመጀመሪያ መርካቶ፤ የክፍለ ሀገር አውቶቡስ ተራ የሚገኝበት፣ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በአገር አቀፍ አልፎም በአፍሪካ ደረጃ ትልቅ የገበያ ቦታ መሆኑን፣ ያካባቢው ነዋሪዎች ከክፍለ ሀገር እየመጡ የሰፈሩ መሆናቸውን ፣ እጅግ በጣም የሚበዙት ደግሞ ሙልጭ ያሉ ድሆች መሆናቸውን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

የትምህርት ቤቱ መምህራን አንዳንድ ተማሪዎችን ጨምሮ ከነዋሪዎቹ 20% እስከ 30% የሚሆኑት በዝሙት ሥራ /የወሲብ ንግድ/ የተሰማሩ መሆኑን ተናግረዋል። ጥናቱ በተደረገበት ጊዜ ት/ቤቱ 2136 ተማሪዎችና 118 መምህራን የነበሩት ሲሆን፣ ከመምህራኑ ውስጥ 30% የሚሆኑት ሴት መምህራን ናቸው። ትምህርት ቤቱ በተጓዳኝ የተዋልዶ ጤና ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን ትምህርቱ ከመምህራንም ከተማሪም ብዙ ተከታይ እንዳልነበረው ተወስቷል።

ለጥናቱ ሁለት የውይይት ቡድኖች ተቋቁመዋል። ከቡድኑ አባላት ሶስቱ መንግሥተዊ ካልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የመጡ ናቸው። ማንኛውም የቡድኑ አባል የሚሰጠው መረጃ በሚስጢር እንደሚያዝለትና ምንም አይነት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ በፈለገው ጊዜ መልቀቅ እንደሚችል ማረጋገጫ ተሰጥቷል።

ብዙ ወጣቶች ጾታዊ ጥቃት ወንጀል ውስጥ እንደሚገኙ በውይይት ቡድኖች ተገልጧል። ባህላዊው የወንድ የበላይነት የሚጀምረው የወጣት ወንዶች አጥቂነት አማላይ ልጃገረዶችን ለወሲብ ሲሉ በመዝለፍ፣ ድንጋይ በማዝነብ፣ ጉልበታቸውን ለማሳየት የልጃገረዶችን ደብተር ወይም ሌላ ንብረት በመቀማት፤ የእነሱን እቃ እንዲሸከሙ በማድረግ፣ በተጨማሪ በፈተና ሰዓት እያስፈራሩ ለጥያቄ መልስ እንዲሰጡ በማስገደድ እንደሚከሰት የቡድኑ አባላት ተናግረዋል።

መምህራን በወሲባዊ ጥቃት ወንጀል ውስጥ እንዳሉበት የታወቀ ቢሆንም ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው መምህራን አንዳቸውም ለመቀበል ወይም መኖሩን ለማረጋገጥ አልፈለጉም- በተለይም ነጥብን (ውጤትን) የጾታዊ ግንኙነት መጠቀሚያ በማድረግ ረገድ። አንዳንድ መምህራን በልጃገረድ ተማሪዎች ላይ ተስፋ የሚያስቆርጥ ቃላት የሚሰነዝሩ መሆናቸው፣ በአለባበሳቸው ምክንያት የሚሰነዝሩት ቃላት ለሰሚ የሚከብድ መሆኑን፣ በተለይ ዳሌያቸውና ጡታቸው ትልቅ በሆኑት ላይ እንደሚብስም ተሰምሮበታል።

- *ወጣቶች ባጠቃላይም ወንዶች አለባበሳቸውንና አቋቋማቸውን እያዩ ሁልጊዜ ልጃገረዶችን ይዘልፏቸዋል፤ ጥቃታቸው በቃላት ብቻ ተወስኖ አይቀርም ጉልበትም ይጨምራል። - ሴት መምህር*
- *ጓደኝነት ጠይቀው እልችልም ሲባሉ ወሳኔህን ለመቀበል ዝግጁ አይደሉም ጉልበታቸውን እስከ መጠቀም ይሄዳሉ። - ሴት መምህር*
- *ልጃገረዶች አስተማሪዎቻቸውን ስለሚፈሩ ያለ ፍላጎታቸው ከማይፈልጉት ሰው ጋር ፍቅር እንዲጀምሩ ይገደዳሉ። - ሴት መምህር*
- *ለምሳሌ አንድ ወንጀል ተፈጽሞ መምህራን እንዲያጣሩ ቢደረግ፣ ከአጣሪዎች አንዱ የሰማውን ሁሉ ወስዶ ይነግረዋል። አጥፊው መረጃውን ለማሳሳት እድል ያገኛል። ሕግ የለም፤ አንተን የሚሰማ ሰው የለም፤ መምህራኑ ጓደኛሞች ናቸው።- ሴት የመያድ አባል*
- *እውነቱን ልንገርህ፤ ብዙዎች ሳይሆኑ ጥቂት እኔ የማውቃቸው መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ጾታዊ ግንኙነት አላቸው። አንድ መምህር ከተማሪው መውለዱን አውቃለሁ።-ወንድ መምህር*
- *ከቤቱ እንድትመጣ ቀጠሮ ይሰጣታል። እሱ ቤት ሔዳ አንድ ነገር ካላደረገች የፈተና ወረቀቷን ላያርመው ይችላል።- ወንድ መምህር*
- *አንዳንድ መምህራን ሴት ተማሪዎቻቸውን ድንገት ከመሬት ተነስተው ይገርፏቸዋል። መምህራኑ ይህን የሚያደርጉት ወሲባዊ ግንኙነት ስለሚፈልጉ ነው። ለምን ይህን ታደርጋላችሁ ብላችሁ ስትጠይቁ የሚሰጧችሁ መልስ መማር ስለማትፈልግና ትምህርት ስለማይገባት ነው ይሏችኋል። - ወንድ መምህር*

ከላይ የተጠቀሱት የመምህራን ቃላት በጥናቱ ጊዜ የተሰበሰቡ ናቸው። ጥናቱ በዚህ አልቆመም። በመምህራንና በተማሪዎች ወይም በወንድና በሴት ተማሪዎች ወይም በትምህርት ቤቱ ዙሪያ በሚያንዣብቡ ወንዶችና ልጃገረዶች መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት የገቢያ ጉዳይ እንደሚሆንም አመልክቷል። በእረፍት፣ በምሳ ሰዓትና ከትምህርት ቤት መውጫ ሰዓት ልብስ ቀይረው ከትምህርት ቤቱ አጥር ጥግ የሚቆሙ ሴት ተማሪዎች እንዳሉ፣ ቀጠሮ የሰጧቸው ወንዶች መጥተው እንደሚወስዷቸው፣ በአካባቢው የሚገኙ ሴተኛ አዳሪዎች ይህን እንደሚያቀላጥፉ ጥናቱ አስረድቷል።

በዚህ ጥናት ወሲባዊ ጥቃት ወንጀል ቢሆንም፣ ተበዳዮቹ መገለልንና መወገዝን በመፍራት በዝምታ የሚቀበሉትና የሚሸከሙት ችግር መሆኑ፣ የወሲብ ጥቃት በትምህርት ቤት የሚበዛ ቢሆንም ኅብረተሰቡ አምኖ ሊቀበለው ያልቻለ ችግር እንደሆነ የእነ አሸናፊ ጥናት አመልክቷል።

አንድን የተፈጸመ ወሲባዊ ጥቃት ወደ አደባባይ ይዞ መውጣትና ማጋለጥ በቤተሰቡ ላይ ሃፍረትንና ውርደትን ማምጣት ሆኖ ስለሚቆጠር፣ ወደ ፍ/ቤት የሚቀርበውም ቢሆን ከበደሉ ጋር የሚመጣጠን ቅጣት ሲሰጥ ስለማይታይ፣ አነ እከሌ ከሰው ምን አገኙ በሚል ተስፋ የሚቆርጠው መብዛቱንም ብዙ ጥናቶች አስረድተዋል።

ስለዚህም ነው ከላይ በመጠኑ ያሳየነውን የጾታ ጥቃት ዋና አገር አቀፍ ችግር አድርጎ በመውሰድ ኢንሺዬቲቭ አፍሪካ ከአራት ዓመት በፊት "ወጣት ልጃገረዶችን ማብቃት" ፤ የሚል ፕሮጀክት የጠነሰሰው ወይም የጀመረው። የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ደግሞ ከእሱ ጎን በመቆም "ደኅንነቱ የተጠበቀ ት/ቤት" ፕሮጀክትን ይዞ በመነሳት፣ ሁለቱ ፕሮጀክቶች እርስ በእርስ ተመጋጋቢ በማድረግ፣ ከላይ የዘረዘርነውን ችግር ለመታገል የተነሱት። በአዲስ አበባ በሚገኘው የስዊድን ኤምባሲ የገንዘብ ድጋፍ የሙከራ ሥራውን በስኬት ያጠናቀቀው ይህ ፕሮግራም ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ለመሸጋገር በመንደርደር ላይ ይገኛል።

ስለ ሁለቱ ፕሮጀክቶች ክንውንና ስለ አስገኙት ውጤት፣ እንዲሁም በመላ አገሪቱ ለማዳረስ ስለተያዘው /የማስፋት/ እቅድ በዝርዝር ወደ ፊት እንመጣበታለን።

ኢትዮጵያ ከ163 ሀገሮች 131ኛ

የአለም የኢኮኖሚና ሰላም ኢንስቲትዩት እ.ኤ.አ በ2019 ባወጣው አመታዊ የሀገራት የሰላም ደረጃ ሪፖርት መሰረት ኢትዮጵያ ሪፖርቱ ከዳሰሳቸው 163 የአለም ሀገራት ውስጥ 131ኛ ወጥታለች። ተቋሙ ደረጃውን ለማውጣት የተጠቀመው መስፈርት ውስጣዊና ውጫዊ ግጭቶች፣ የህዘብ መፈናቀል፣ ብጥብጥ፣ የወንጀል ድረጊቶች፣ ሽብር፣ የጦር መሳሪያ ዝውውርና አጠቃላይ የማህበረሰብ ጸጥታና ደህንነት ጉዳዮችን ነው።

ተቋሙ እ.ኤ.አ በ2016 ባወጣው ሪፖርት ኢትዮጵያ 119ኛ ደረጃ የነበራት ሲሆን ከነበረችበት 12 ሀገራት ቀድመዋት ወደ ኋላ በመሄድ በዚህ አመት 131ኛ ደረጃ ይዛለች። በመሆኑም ኢትዮጵያ በሰላም ይዞታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ካላቸው 44 ከሰሀራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት የምትበልጠው 11 ሀገራትን ብቻ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ እንደ ሶማሊያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ማእከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ኒጀር፣ ማሊ፣ ቻድና የመሳሰሉት ሀገራትን ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ የሰላም ይዞታቸው ካዘቀዘቀ 27 የሰሀራ በታች የአፍሪካ ሀገሮች ምድብ ውስጥ ተካታለች።

በሰላም እጦት በከፍተኛ ሁኔታ ግንባር ቀደም ተጎጂዎች ደግሞ ህጻናትና ሴቶች ናቸው። አለም አቀፍ መረጃዎችም ይህን ሀቅ ያጠናክራሉ። ስለዚህ ኢትዮጵያ በሰላም ረገድ ከ163 የአለም ሀገራት 131ኛ ወጣች ሲባል ጉዳዩ ከቁጥር ጨዋታ አልፎ የበርካታ ኢትዮጵያውያን እናቶች፣ ልጃገረዶችንና ህጻናትን ህይወት የሚመለከት መሆኑን ልብ ይሏል።

GLOBAL PEACE INDEX 2019



‹‹ሴቶች ብቻ - only Women››

ሀና ጌታቸው

የመጸዳጃ ቤት ችግር በሴቶች ይብሳል ውይስ በወንዶች? ደሞ ይሄ ምን አይነት ጥያቄ ነው ያስብላል? በአዲስ አበባ ከተማ የመጸዳጃ ቤት ችግር ለሴት ለወንድ ሳይባል ለሁሉም ችግር መሆኑ ባይካድም ችግሩ ግን በሴቶች ዘንድ የጠና ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ አንዲት ሴት ውሀ ሽንት ቢያጣድፋት የት ትገባለች? ሆቴሎች፣ ቡና ቤቶችና መጠጥ ቤቶች የመጸዳጃ ቤቶቻቸውን ይቆልፋሉ። የማይቆለፋት ወይም ክፍት ቦታ የሚገኙት ለወንዶች የውሃ ሽንት መጠቀሚያ የሚያገለግሉት ብቻ ናቸው። አንዳንድ ትላልቅ ሆቴሎች መጸዳጃ ቤቶቻቸው ክፍትና ለሴቶች ንጹህና ምቹ ቢሆኑም ለአብዛኛዎቹ የከተማችን ሴቶች ተደራሽ አይደሉም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከተማ አስተዳደሩ በአንዳንድ የከተማዋ ጎዳናዎች ዳርቻ የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች ተከፍተው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። እነዚህ በክፍያ ደንበኞቻቸውን የሚያስተናግዱ መጸዳጃ ቤቶች ለተወሰኑ የከተማው ነዋሪዎች እፎይታን ቢሰጡም ቁጥራቸው በቂ ባለመሆኑና በሙሉ አቅማቸው የማይሰሩ በመሆናቸው በተለይ የሴቶችን ችግር ከማቃለል አንጻር ገና ብዙ ይቀራቸዋል። በዚያ ላይ በውሀ እጥረትና በአስተዳደር ድክመት ምክንያት ለሴት ተገልጋዮች በሚያረካ መልኩ አገልግሎት እየሰጡ አይደለም።

የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን ባወጣው መረጃ መሰረት በ2007 እና በ2008 ዓ.ም በ148 ሚሊዮን ብር ወጪ 313 የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች አስገንብቶ አገልግሎት ላይ ማዋሉን ጠቅሶ መጸዳጃ ቤቶቹ ከታሰበላቸው አገልግሎት ውጪ በመዋላቸውና ንጽናቸው ባለመጠበቁ ቅሬታውን ገልጾ እርምጃ እንደሚወስድ አመልክቷል።

እናም በአዲስ አበባ ከተማ ከቤቷና ከመስሪያ ቤቷ ውጪ ሆና የውሀ ሽንት ያስጨነቃት ሴት ፈተና ውስጥ ትወድቃለች፡፡ ወንዱ እንዲህ አይነት ሁኔታ ቢገጥመው ወደ አንዱ ስርቻ ጠጋ ይልና ቧንቧውን መክፈት ይችላል። ግፋ ቢል <<ወንድም እንዴት እዚህ አካባቢ ትሸናለህ?>>የሚል የደንብ አስከባሪዎችና የመንደር ጎረምሶች ቁጣና ግሳጼ ቢደርስበት ነው። ከጭንቅ የተገላገለውም ሰውዬ <<ይቅርታ ! ሽንቴ ወጥሮኝ ነው።>> በሚል ምላሽ ነገሩን ይቋጨዋል። ጫን ካለም አምስት ወይም አስር ብር ቢቀጣ ነው።

በውሃ ሽንት የተጨነቀች የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወይም ከሌላ የሀገሪቱ ክፍል የመጣች ሴት ግን ወንዱ እንደሚያደርገው ከአንዱ ጥግ ቁጢጥ ብላ ጭንቀቷን ልትገላገል አትችልም። በአስገዳጅ ሁኔታ ብታደርገው እንኳ <<ምን ያለችው ባለጌ ነች? ትንሽ እንኳ አታፍርም?>> ከሚለው ትችት አንስቶ ዘለፋ፣ ስድብና በአንዳነድ ስፍራም አካላዊ ጥቃትም ሊደርስባት ይችላል።

ስለዚህም ሴቶች በከተማው ባለው የመጸዳጃ ቤት ችግር ምክንያት ተፈጥሯዊ ባልሆነ መልኩ ውሃ ሽንታቸውን ለመቋጠር ይገደዳሉ። ይህም ጸረ - ተፈጥሯዊ ልማድ በርካታ ሴቶችን ለሽንት ፊኛ ኢንፌክሽን ሲዳርጋቸው ይስተዋላል። ከሁሉም የሚብሰው ደግሞ ሴቶች በውሀ ሽንት ውጥረት ላለመጨናነቅ ሲሉ የሚጠጡትን ፈሳሽ በእጅጉ መቀነሳቸው አንዳንዶችም ውሀ መጠጣትን መተዋቸው ነው። ይህ ልማድ በቤታቸውም ሆነ በስራ ላይ ሆነው ቀጣይነት ስለሚኖረው ውሀን ያለመጠጣት ቋሚ ልማድ ሆኖ ይቀራል። በቂ ውሃ ወይም ፈሳሽ ያለመውሰዳቸው ደግሞ ለኩላሊት በሽታ ይዳርጋቸዋል። ለዚህም ነው ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በኩላሊትና በሽንት ፊኛ ኢንፌክሽን የሚሰቃዩት። እዚህ ላይ በጥናት የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ ለጊዜው ባይቻልም የገሀዱን አለም እውነታ በምንኖርበትና በስራ አለም ያሉትን ሴቶች በማጤን መረዳት እንችላለን።

እናም በአዲስ አበባ ከተማ የመጸዳጃ ቤት ችግር ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ ይህን መሰል ችግር የሚያስከትል ከሆነ ምን መደረግ አለበት ወደሚለው ይወስደናል። ጉዳዩ ህብረተሰቡን፣ መንግስትንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ሁሉ የሚመለከት ቢሆንም እስቲ የመፍትሄ ሀሳብ በመሰንዘር መጀመሪያ ውይይት በመቀጠልም ለድርጊት ተነሳሽነት አንድ ሁለት እንበል። በከተማው ውስጥ አሁን በየሰፈሩ እንደተገነቡት የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች ያሉ በክፍያ ሴቶችን ብቻ የሚያስተናግዱ መጸዳጃ ቤቶች ቢገነቡ ምን ይመስላችኋል?

ልብ ብላችሁ አስተውላችሁ ከሆነ አሁን በከተማው ውስጥ ባሉት የህዝብ መጻዳጃ ቤቶች በአብዛኛው የሚጠቀሙት ወንዶች ናቸው። በነዚህ መጸዳጃ ቤቶች የሚገለገሉ ሴቶች ቁጥራቸው ጥቂት ነው። ሴቶች እነዚህን መጸዳጃ ቤቶች የሚጠቀሙት እጅግ አስገዳጅ ሁኔታ ሲገጥማቸው እንጂ ውሀ ሽንታቸውን መቋጠር እስኪቻሉ ድረስ በነዚህ መጸዳጃ ቤቶች ላለመጠቀም ይታገላሉ። በዚያ ላይ አንዳንድ ስነ ምግባር የሌላቸውና አዋኪ ወንዶች የሚያደርሱባቸውም ተጽእኖ መጸዳጃ ቤቶችን ከመጠቀም ያርቋቸዋል። ስለዚህ ‹‹ሴቶች ብቻ - only Women›› የሚሉ የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች ቢገነቡ አሪፍ አይደለም?

የሞዴስ ነገር



ሀና ጌታቸው

የሰሞኑን የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ (ሞዴስን) በተመለከተ ከጤና ሚኒስቴር አንድ ዜና ተሰራጭቶ ነበር። ዜናው የወር አበባ የንፅህና መጠበቂያ ምርት የህክምና ቁሳቁስ አካል ሆኖ በኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ቁጥጥር ባለስልጣን የክትትል ዝርዝር ውስጥ መካተቱን የሚገልጽ ነው።

ዜናው አያይዞም በትምህርት ቤት፣ ክሊኒኮችና በጤና ተቋማት የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሱን በማቅረብም የአፍላ ልጃገረዶችን የጤና ተደራሽነት ለማሳደግ አዲስ መርሀ ግብር ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሶ በገጠር ከሚኖሩ አፍላ ወጣቶች መካከል በርካታ ልጃገረዶች የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ መረጃና እውቀት እንዲሁም ሞዴስ ባለማግኘታቸዉ ከትምህርት ገበታቸው እንደሚቀሩና ለስነልቦና ችግር እንደሚጋለጡ ያብራራል።

እስቲ <<ሞዴስ ባለማግኘታቸዉ ከትምህርት ገበታቸው እንደሚቀሩና ለስነልቦና ችግር እንደሚጋለጡ>> የሚለውን ሀሳብ እናስተውል። አንዲት የገጠር አፍላ ወጣት ሞዴስ ባለማግኘቷ ብቻ ትምህርት ስታቋርጥና ለስነ ልቦና ችግር ስትጋለጥ ማየት ስሜት የሚነካ ገጠመኝ ነው። ወደ ፊት በእውቀት ዳብራ እራሷን ለውጣ ለወገን ለሀገር የምትተርፍ ዜጋ ሞዴስን በመሰለ ቁሳቁስ ምክንያት ህይወቷ ሲበላሽ ማየት እንደ ማህበረሰብም እንደ መንግስትም የሚያሳስብ ጉዳይ ነው።

እዚህ ላይ የፈረደበት ድህነታችን፣ የማስፈጸም አቅም ድክመታችንና ትኩረት ያለመስጠት ችግር ይጠቀስ ይሆናል። << ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም>> እንደሚባለው ግን ከልብ ካሰብንበት ለዚህ ችግር መላ አይጠፋም። በዜናው መጨረሻ ላይም <<ይህንን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የጤና ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ሴክተር ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት እነዚህን ተጋላጭ ልጃገረዶች በትምህርት ቤት መቆየት እንዲችሉ ለማድረግ የአጭርና የረጅም ግዜ እቅዶች አውጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ>> ተገልጿል።

ጥረቱ ይበል የሚያሰኝ ነው። <<ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም>> የሚባለውም ይህ ነው። ሌሎች የመንግስት አካላትም የጤና ሚኒስቴርን አርአያነት ተከትለው ካሰቡበት መላ ለማይጠፋለት ችግር መላ ይምቱ እንላለን።

ሴቶችን ለውሳኔ ሰጪነት ለማብቃት የሁሉንም ርብርብ ይጠይቃል

እሸቱ ደስታ

ከጠቅላላው የህብረተሰብ ክፍሎች ከግማሽ በላይ ድርሻ ያላቸው የሃገራችን ሴቶች ናቸው። የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ደግሞ ችግሮቻቸውን በሚፈለገው ደረጃ በመፍታት ረገድ ውስንነቶች እንዳሉ ያሳያል።

ሴቶችን ለማብቃት የውሳኔ ሰጪነት ሚናቸውን በማሳደግና የፖለቲካ ተሳትፎን በማጎልበት በሁሉም የልማት ዘርፎች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሁም ለሀገሪቱ ልማት እና እድገት መሰረት እንዲሆኑ ማድረግ የግድ ይላል።

ከዚህ አንፃር የሴቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት መ/ቤቶች የሴቶች ጉዳይ መዋቅሮች የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት በሚያስችል ቁመና ላይ ያለመገኘታቸው እንዲሁም በየተቋማቱ የሚገኙ የበላይ አመራሮች በተገቢ ሁኔታ የሚመሩበትና የሚገመገሙበት የአሰራር ስርዓት ያለመጠንከሩ እንደክፍተት ታይቷል ይላል መጋቢት 2009 የወጣው የኢትዮጵያ ሴቶች የልማት እና የለውጥ ስትራቴጂ ሰነድ።

ሰነዱ ከዚህ በመነሳት የሴቶችን ተሳትፎ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ሂደት የተለዩ ቁልፍ ችግሮች በሚለው ስር በየደረጃው ያለው አመራር ቁርጠኝነት ማነስ በሁሉም አካላት የአቅም ውስንነት መኖር፣ የተጠያቂነት አሰራር አለመጠንከር፣ ስራ አጥነት እና ለሴቶች ተስማሚ አገልግሎቶች አለመስፋፋትንም ይጠቁማል።

በዚህ ረገድ ሴቶችን ወደ ኃላፊነት ለማምጣት ያሉ ተግዳሮቶች እና ምቹ ሁኔታዎችን በተወሰነ ደረጃ መጥቀሱ ጠቃሚ ነው። በዚህም ለሀገራችን ምቹ ሁኔታዎችን መመልከት ቢያስፈልግ ፖለቲካዊ ምቹ ሁኔታዎች፣ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው እና የተፈራረመቻቸው ህጎች መኖር በቁጥር ጥቂት የሆኑ መልካም ወንዶች መኖር እና በከተማ የተማሩ እና እችላለሁ የሚሉ ሴቶች ቁጥር መጨመር ተጠቃሽ ናቸው። ለዚህም እንደአብነት የሚቀርበው በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ካሉት 20 የካቢኔ አባላት አስሩ ወይም 50 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸው እንዲሁም የሀገሪቱ ፕሬዚደንት፣ የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚደንት እና የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው የተሾሙት እንዲሁ ሴቶች መሆናቸው ነው።

ሌላው በሃገራችን ሴቶችን ወደ ኃላፊነት ለማምጣት ካሉት ተግዳሮቶች መካከል አባታዊ ስርዓት ሊቀር አለመቻሉ፣ ባህላዊ አመለካከት፣ ቤተሰብን መምራት፣ ህጻናትን መንከባከብ፣ በማህበራዊ ጉዳዮች የመሳተፍ (ዕድር፣ ዕቁብ....) እንዲሁም ተቀባይነትን ማጣት፣ አትችልም መባልና ከሚጠበቀው በላይ ሰርታ ማሳየት ይሆናል። ለዚህም እንደምሳሌ የሚጠቀሰው በፌደራል ደረጃ የካቢኔው ቁጥር 50 በመቶ ሴቶች ይሁን እንጂ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ በጣም ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ ሴቶች ናቸው በኃላፊነት ላይ ያሉት።

ይህንንም ችግር ለመቅረፍ እንደመፍትሄ ከሚጠቀሱት መካከል አንዳንዶቹ እንደሚከተለው ተጠቁመዋል፡-

- ሴቶችን ወደአመራርነት ወይም ውሳኔ ሰጪነት ለማምጣት ራሳቸውን ማዘጋጀት እና ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል። ለዚህም ወንዶች ሊረዷቸው፣ ሊያግዟቸው የግድ ይላል።
- ጥሩ የሰሩ ሴቶችን የማበረታታት ሁኔታ በስፋት ስለማይታይ ይሄ ትኩረትን ይሻል።
- በየጊዜው ሴቶች ላይ ብዙ ገንዘብ እና እውቀት ፈሶበት ጥናት ተደርጎ መፍትሄ ተቀምጦለት በቢሮ ከሼልፍ ውስጥ ከመቀመጥ ውጪ ውጤት ያላመጡትንም ጥናቶች በየጊዜው መፈተሽ እና ወደተግባር ማሸጋገር ያስፈልጋል።
- በሴቶች ላይ የወጡ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች በተግባር እየተተረጎሙ አይደለም። ሰፊ ክፍተት አለ። በዚህም በገጠር እና በከተማ የሚገኙ ሴቶች በእኩልነት መብታቸው ያልተጠበቀው በዚህ የተነሳ ስለሆነ ትኩረት ይሻል።
- በሃገራችን ከላይ እስከታች በየደረጃው የሴቶች ጉዳይ በሚል የተዋቀሩት አካላት ከንግግር ባለፈ የሴቶችን እኩልነት ወይም ለኃላፊነት እንዲበቁ የሚደረገው ስራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።
- በሃገራችን ሴቶችን በማህበር፣ በሊግ፣ በፌዴሬሽን እና በመሳሰሉት የማደራጀት ተግባር በነፃነት ያለማንም ጣልቃ ገብነት የሚደራጁበት ሁኔታ ቢመቻች ይመረጣል።

የጾታ እኩልነት ሂሳብ

ሀና ጌታቸው

<<ደሞ የጾታ እኩልነት ሂሳብ አለ እንዴ?>> ትሉ ይሆናል። አዎ አለ። አንዲት ሀገር በጾታ እኩልነት ያላት ደረጃ በሂሳብ ይሰላል። በዚህ ሂሳብ መሰረትም በየአመቱ ሀገራት በጾታ እኩልነት ያላቸው ደረጃ ተሰልቶ ይቀርባል። በዚህም መስፈርት ደረጃ የበለጸጉት ሀገራት ሁሌም ከራስጌ ሲገኙ እንደ ኢትዮጵያ ያሉት ያላደጉ ሀገራት ደግሞ ከግርጌ ይገኛሉ።

የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም የሰብአዊ ልማት ሪፖርት እንደሚያመለክተው የአንድ ሀገር የጾታ እኩልነት ደረጃ ምን እንደሚመስል ለመመዘን ሦስት አበይት መስፈርቶች በዋነኝነት ስራ ላይ ይውላሉ።

1. ጤና

በጤና ዘርፍ መጀመሪያ የሚታየው የወላድ እናቶች ሞት ነው። ስለዚህም ከ100ሺ ወላድ እናቶች ውስጥ ምን ያህል እናቶች በወሊድ ወቅት ሞቱ የሚለው ይሰላል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚታየው የወጣት ሴቶች ወሊድ ነው። በዚህም ረገድ እድሜያቸው ከ15 – 19 ካሉ 1ሺ ወጣት ሴቶች ውስጥ ምን ያህሉ ወለዱ የሚለው ይታያል።

2. ሴቶችን ማብቃት

ሴቶችን ከማብቃት አኳያ የመጀመሪያው የሚታየው ሴቶች በሀገራቸው ፓርላማ ውስጥ የያዙት የመቀመጫ ብዛት ነው።

ሁለተኛው ደግሞ እድሜያቸው 25 እና ከዛ በላይ ከሆኑት የአገሪቱ ዜጎች ውስጥ ምን ያህል ሴቶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አጠናቀዋል የሚለው ነው።

3. የሥራ መስክ ተሳትፎ

እድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ ሆነው በስራ መስክ ከተሰማሩት የሀገሪቱ ዜጎች ውስጥ በሴቶች የተያዘው የሥራ መስክ ምን ያህል ነው የሚለው የሀገሪቱን የጾታ እኩልነት ለመመዘን ጥቅም ላይ ይውላል።

በነዚህ መስፈርቶች መሠረት እ.ኤ.አ በ2018 የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም የጾታ እኩልነት ሪፖርት መሠረት ኢትዮጵያ ከ178 ሀገራት 173ኛ ነው የወጣችው። የ2019 ሪፖርትም ከዚህ የተሻለ እንደማይሆን መገመት ይቻላል።

በጣም የሚገርመው ግን በሀገሪቱ ከቀደምት ፖሊሲዎች መካከል አንዱ የሆነውና በ1986 ዓ.ም በሽግግር መንግስት ጊዜ የወጣው ብሄራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ ነው። የኢትዮጵያን ሴቶች መብት ለማስከበር እ.ኤ.አ በ1979 የወጣውን በሴቶች ላይ የሚፈጸም መድልዎ የማስወገድ አለም አቀፍ ስምምነትን ጨምሮ በተለያዩ ጊዜያት የወጡ አምስት አለም አቀፍ ስምምነቶችንና አዋጆችን ሀገሪቱ ተግባራዊ ለማድረግ ተቀብላለች። ግን ምን ጠብ ያለ ነገር አለ?

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የካቢኔያቸውን 50 በመቶ በሴት ሚኒስትሮች ቢያሲዙም ይህ ጅምር ግን በየደረጃው ወደታች አልወረደም። በርግጥ እንደ ኢትዮጵያ ባለች ድሀና ኋላ ቀር ሀገር የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ በርካታ አቀበቶችን መውጣት ይጠይቃል። ይህም ሁሉ ሆኖ ግን ከሀገሪቱ 110 ሚሊዮን የሚገመት ህዝብ ውስጥ 55 ሚሊዮን የሚሆኑትን እናቶቻችንን፣ እህቶቻችንን፣ ሚስቶቻችንንና ልጆቻችንን ወደ ጎን ትተን ልማትና እድገት የለምና የሚመለከተው አካል ሁሉ ባልሰማ ባላየ ጉዳዩን ማቀዝቀዝ አይችልም።

የጀበና ቡና

ዮሀንስ ታሪኩ

የጀበና ቡና ሲባል ወደ አእምሯችን የሚመጣው ምስል ረከቦት ላይ የቡና ሲኒ ተደርድሮ፣ ኩልል ያለ አቦል ቡና ሲቀዳና እጣኑ ሲትጎለጎል ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ ግን ልናነሳ የወደድነው በየመንገዱ ዳር ስለሚሸጠው የጀበና ቡና ነው። የጀበና ቡና እንዲህ አገር ምድሩን ካጥለቀለቀው ምን ያህል ጊዜ ሆነው? ምን አልባት አስር አመት ቢሆነው ነው።

በሀገር ውስጥ የሚመረተው ቡና በሁሉም ስፍራ በባህላዊ ጀበና ተፈልቶ ለተጠቃሚው መቅረቡ መልካም ነው። ለበርካታ እህቶቻችንና እናቶቻችንም የስራ እድል ፈጥሮላቸዋል። የኑሮ ውድነት የደቆሰው ከተሜም በአነስተኛና በተመጣጣኝ ዋጋ የቡና አምሮቱን እየተወጣ ነው።

ግን ግን የጀበና ቡና አፍይውን ብዛት ልብ ብላችኋል? በአንዳንድ የከተማችን ስፍራዎች በየአምስት ሜትሩ ርቀት ላይ የጀበና ቡና ይገኛል። በአንዳንድ ቦታ ደግሞ እጅግ ከመቀራረባቸው የተነሳ ቡና አፍዮቹ ደንበኛ በማያስተናግዱበት ወቅት የሞቀ ወግ ይዘው ይታያሉ። በረከቦታቸው ላይ ሲኒዎችን ደርድረው፣ የፈላው ቡና ጢሱ ቡልቅ እያለ አጠገብ ላጠገብ ያሉት ቡና አፍዮች ከመንገድ ዳር የደራ ጨዋታ ይዘው ላያቸው ያስገርማሉ። እውነት እነዚህ በየአምስት ሜትሩ ርቀት ግራና ቀኝ ረድፍ ይዘው የጀበና ቡና የሚያፈሉ እህቶቻችን በቂ ደንበኞችን ያገኛሉ? ከዚህ ስራ ትርፍ ያገኛሉ? አትርፈውስ ኑሯቸውን መምራት ይችላሉ? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት መቼም መለስተኛ ጥናት ሳያስፈልግ አይቀርም። ጥያቄዎቻችንን በሙሉ በጥናት መመለስ ስለማንችል ለጊዜው ጉዳዩን በአስተውሎት ( ) እንቃኘው።

የመጀመሪያዎቹን የጀበና ቡና አፍይዎች ስራ ፈጣሪዎች ልንላቸው እንችላለን። ምክንያቱም ከመኖሪያ ቤት ውጪ ተጠጥቶ የማያውቀው የጀበና ቡና አደባባይ ሲወጣ ጠጪ ያገኛል ብሎ የቢዝነስ ፕላን ማውጣት የስራ ፈጣሪነትን ተሰጥኦ ይጠይቃል። እናም ግንባር ቀደሞቹ የጀበና ቡና አፍዮች እየወደቁ እየተነሱ፣ እየከሰሩ እያተረፉ ገበያውን ፈጠሩት።

መቼም የሀገራችን ሰው እንደ ቦይ ውሃ በተቀደደለት መፍሰስ ይወዳልና << አሀ! ቡና በጀበና አፍልቶ መሸጥ ማን ያቅተዋል?>> ወደ ጀበና ቡና ገበያ አንዷ አንዷን እያየች ተግተልትለው ገቡ። በዚያ ላይ የጀበና ቡና ቢዝነስ ለመጀመር የሚያስፈልገው ገንዘብ አነስተኛ ነው። ደግሞም የሆነ ጥግ ላይ ከለላ ነገር አበጅቶ ረከቦት ላይ ሲኒዎችን ደርድሮ መቀመጥ ይቻላል። ይህ ሁሉ ምቹ ሁኔታ ወደ ጀበና ቡና ገበያ ዘው ብሎ ለመግባት ጉዳዩን የቁልቁለት መንገድ እንዳደረገው በቢዝነሱ የተሰማሩ እህቶቻችን ይገልጻሉ።

እንግዲህ የጀበና ቡና አነስተኛም ቢሆን ያው ቢዝነስ ነው። እህቶቻችን ስራ ብለው ይዘውት ከማለዳ እስከ ምሽት ድረስ ውለው ይገቡበታል። በዚህ የስራ መስክ የተሰማሩት እህቶቻችን ስብጥር ሲታይ የሚያስገርም ነው። አረብ ሀገር ሄዳ ያልተሳካላት፣ ሻል ያለ ንግድ ጀምራ የከሰረች፣ ከባሏ ተፋታ የኑሮን ትግል ብቻዋን የጀመረች፣ ለተሻለ ህይወት ከገጠር ኮብልላ የመጣች፣ የጀመረችው የውጭ ሀገር ፕሮሰስ እስኪሳካ መደበሪያ ይሆነኛል ብላ ያመነች፣ ወደ ተሻለ ቢዝነስ ለመሸጋገር አንገት ማስገቢያ ይሆነኛል ያለች፣ በነበረው የትምህርት ፖሊሲ ከአስረኛ ክፍል በኋላ ወዴትም መፈናፈኛ ያጣች፣ የእለት ጉርስ ያጣችና ዙሪያው ገደል የሆነባት ሁሉ በዚህ እንደ አሸን በፈላው የጀበና ቡና ስራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ።

ይበልጥ ሆድ የሚበላው ክስተት ግን ደረጃቸው ከጀበና ቡና ቢዝነስ በላይ ሆነው አማራጭ በማጣትና በልተው ለማደር ሲሉ ብቻ በዚህ ስራ ውስጥ የሚዳክሩት እህቶቻችን ናቸው። በዚህ ስራ ውስጥ በርካታ ባለዲግሪ እህቶቻችን እንዳሉ ታውቃላችሁ? የሚያሳዝነው ነገር ሰርተው መብላታቸው አይደለም። የሚያሳዝነው ሀገሪቱ በተሰማሩበት የሙያ መስክ ልታሰማራቸው ስላልቻለች እውቀታቸው ባክኖ መቅረቱና ተስፋ የለሾች መሆናቸው ነው። በዚያ ላይ ይህን ስራ መሸጋገሪያ እንዳያደርጉት በገበያው ውስጥ ከሚራኮቱት ወፈ ሰማይ እህቶቻችን ውስጥ ልቆ ለመውጣት ፈተናው የእዮብን ትግስት የሚጠይቅ ነው።

ግን እነዚህን እህቶቻችንን ዝም ብለን ነው የምናያቸው? እንዴት ይሄንኑ ስራ ወደ ተሻለ ቢዝነስ የሚያሳድጉበት መላ አይፈለግም? አንዲት በጀበና ቡና ስራ የተሰማራች ልጅ አውቃለሁ። ልጅቷ መልካም ጣዕም ያለው ቡና ስለምታፈላ በርካታ ደንበኞች አሏት። የቡናዋ ጥራት ከእለት እለት የማይቀያየር በመሆኑ በደንበኛ ላይ ደንበኛ እየጨመረች ነው የምትሄደው። ታዲያ ምን ያደርጋል የምትሰራበት ቤት ስፋት ከአራት ካሬ ሜትር ስለማይበልጥ ቢዝነሷ ሊፋፋ አልቻለም። በከተማችን ለእንደዚህ አይነቷ ታታሪ ወጣት የሚሆን በርካታ የባከኑ ስፍራዎች ቢኖሩም ለነዚህ እህቶቻችን ያሰበላቸው አካል የለም። በየመድረኩ ግን <<ለወጣቱ የስራ እድል ለመፍጠር ...>> የሚል ዲስኩር መስማት ወጣቱን አታክቶታል።

ምንም ሆነ ምን እህቶቻችን ስራ ፈጥረዋል። እሬት እሬት ከሚል የማሽን ቡና ገላግለውናል። ዋጋውም ኪስ ስለማይጎዳ በቀን ሁለት ሶስት ሲኒ የጀበና ቡና እንጠጣለን፤ ያውም እጣን ተጭሶልን ጤና አዳም ተጨምሮልን። በዚያ ላይ ዋጋ የማይተመንለት ትሁት መስተንግዷቸውም አንጀት ይበላል። ነገ ቀን ይወጣልኛል ብለው አንገታቸውን ሰብረው፣ የሁከት ፈጣሪውን ወንድ ትንኮሳና ጥቃት ተቋቁመው በየእለቱ ይታትራሉ። ሸክማቸውን ለማቅለልና ነገን በተስፋ እንዲጠብቁ ግን ከህብረተሰቡ፣ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ምን ተደረገላቸው? ምንም!

ባህላዊ የስፌት ዕቃዎች

ከዚህ በታች የምትመለከቷቸው ባህላዊ የስፌት ዕቃዎች በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍሎች ለቤት ውስጥ መገልገያነት የሚውሉ የዕደ ጥበብ ውጤቶች ናቸው። የዕደ ጥበብ ውጤቶቹ በሴቶች የሚሰሩ ሲሆን አንዳንዶቹን ጨርሶ ለማጠናቀቅ ከወር በላይ ሊወስድ ይችላል።

እነዚህን የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ለመስራት የሚያስፈልጉ ግብአቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ሰበዝ
- ስንደዶ
- አለላ
- ወስፌ

ሰበዝ፣ ስንደዶና አለላ ጊቻ ከተባለ የሳር ዝርያ የሚገኙ ሲሆን ጊቻ የሳር ዝርያ በአብዛኛው የሀገሪቱ ደጋና ወይናደጋ ስፍራዎች የሚበቅል ነው። ሰበዝ ጊቻ ሳሩን በማጨድ ይሰበሰባል። ስንደዶ ግን ጊቻ ሳሩ ከመታጨዱ በፊት በመስከረምና በጥቅምት ወራት ረጃጅሙን አክርማ በመቅጨት የሚገኝ ነው። ስንደዶው በውሀ ርሶ ለሁለት ይሰነጠቅና ሰበዙን አያይዞ ለመስፋት ጥቅም ላይ ይውላል።

የተሰነጠቀው ስንደዶ በቀለም ሲነከር አለላ ይባላል። አለላ የስፌት ስራዎቹን ዲዛይን ለመስራትና ለማስዋብ ይጠቅማል። በተለይ በግድግዳም ላይ ይሁን በጠረጴዛ ላይ ለጌጥ የሚቀመጡት እንደሙዳይና ቆለምሻሾ የመሳሰሉት የስፌት ስራዎች በተለያየ ቀለም በተነከሩ ስንደዶዎች (አለላዎች) የተሰሩ ናቸው።

ስለነዚህ የሀገራችን የዕደ ጥበብ ውጤቶች ስናወራ ግን በፍጹም የማይዘነጉ የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ - ሴቶችና ልጃገረዶች። ሴቶችና ልጃገረዶች ሰበዙን፣ ስንደዶውንና አለላውን ከማዘጋጀት ጀምሮ የስፌት ስራው ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሙሉ ተሳትፎ ያደርጋሉ። በአጭሩ አነጋገር ይህ የዕደ ጥበብ ዘርፍ ሙሉ በሙሉ የሚከናወነው በሴቶች ነው።

የሀገራችን ሴቶች እነዚህን ውብ የዕደ ጥበብ ውጤቶች በብዙ ብልሀትና ልፋት ካመረቱ በኋላ ያዘጋጁትን ምግብ በነዚህ መገልገያ ዕቃዎች ላይ አድርገው ገበታ ያቀርባሉ። መገልገያ ዕቃዎቹ ከተፈጥሮ ሳር የሚሰሩ በመሆናቸው ምግብን ለመመገቢያና ሳይበላሹ ለማቆየት ተመራጭ ናቸው። በከተሞች ጭምር እንጀራ የሚቀመጠው በመሶብ ነው። በመሶብ የተቀመጠ እንጀራ አይሻግትም። የሃገራችን ቆሎ፣ ንፍሮ፣ ቂጣ፣ አንባሻ፣ ድፎ ዳቦ፣ እንጎቻ፣ አነባበሮ፣ እንጀራ በወጥና ሌሎች ባህላዊ ምግቦች ሁሉ የሚቀርቡት በነዚህ የዕደ ጥበብ ውጤቶች ነው።

ኸረ ለመሆኑ ከዚህ በታች ምስላቸው ከቀረቡት የስፌት እቃዎች ውስጥ ምን ያህሉን በስምና በግብር እናውቃቸዋለን?

1. መሶብ - መመገቢያ እቃ (በተለይ በድግስ ወቅት)
2. ሌማት - መመገቢያ እቃ
3. ሰፌድ - እንጀራ ከምጣድ ማውጫ፣ ጥራጥሬና እህል ማበጠሪያና ማንፈሻ
4. ዝንበ ከልክል መሶብ - እንጀራ ማስቀመጫ (ማከማቻ)።
5. እንቅብ - ከ25 እስከ 50 ኪሎ እህልና ጥራጥሬ ሊይዝ የሚችል እቃ። የሚቆላ ጥራጥሬን ከምጣድ እያወጡ ለማጠራቀም፣ የተፈጨን ዱቄት ከቋት እያወጡ ለማጠራቀምና የሚሸጡ የግብርና ምርቶችን ተሸክሞ ገበያ ለመውሰድ ያገለግላል።
6. ወንፊት - ዱቄት፣ ጤፍና የመሳሰሉትን ለመንፋትና ለማጣራት ያገለግላል።
7. ቁና - እህል፣ ዱቄትና የመሳሰሉትን ለመስፈር ያገለግላል።
8. አገልግል - የበሰለ ምግብ እንደ ስንቅ ለማጓጓዝ ያገለግላል።
9. ሙዳይ - ጌጣጌጥ፣ ገንዘብና ውድ ንብረቶችን ለማስቀመጥ ያገለግላል።
10. እርቦ (ቆለምሺሻ) - ቆሎና ንፍሮ ለማቅረብ ያገለግላል።
11. ቆለምሺሻ - እንደ ፈንዲሻ ያሉ ቆሎዎችን ለማቅረብና ግድግዳ ላይ ተሰቅሎ እንደ ጌጥ ያገለግላል።
12. ባለ እፊያ (ክዳን) ቆለምሺሻዎች - ቅርጻቸው እንደ መሶብ ሆኖ በመጠን ግን ትናንሽ ናቸው። በተለይ እንደ ጉራጌ ባሉ የደቡብ አካባቢዎች ክዳን ያላቸውና የሌላቸው ተደርገው የሚሰሩ ሲሆን ቆሎ ለማቅረብ ያገለግላሉ።

እነዚህ ለሺ አመታት በሀገራችን ሲመረቱና አገልግሎት ሲሰጡ የኖሩት የስፌት ዕቃዎች ደረጃ ወጥቶላቸው በፋብሪካ ባይመረቱም ከመገልገያ ዕቃነታቸው በተጨማሪም የወግ ዕቃዎች ሆነው በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ውስጥ የራሳቸው ድርሻ አላቸው። ዋጋቸውም ኪስ ስለማይጎዳ ድሀ የተባለ ቱሪስት እንኳ ሊገዛቸው ይችላል። በኢኮኖሚው ዘርፍ እነዚህ የስፌት ስራዎች ይበልጥ ተውበውና ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲመረቱና ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቢታሰብበት መልካም ነው።

ሌላው እነዚህ የዕደ ጥበብ ውጤቶች በየብሔረሰቡ ባህልና ትውፊት ውስጥ ቦታ ያላቸው መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። በየተረቱ፣ በተረትና ምሳሌው፣ በግጥሞችና በዘፈኖች ውስጥ እነዚህ የቤት ውስጥ መገልገያዎች ይጠቀሳሉ። አንዳንዶቹን እንጥቀስ

- የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ
- ያለላ ሙዳይ ኮለል ኮለል በይ
- በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም
- ለስሟ መጠሪያ ቁና ሰፋች
- ቁና ቁና ተነፈሰ
- እገሌ የወንዶች ቁና
- ሺ ዝንብ መሶብ አይከፍትም
- ሰፌድ እግር
- ሰፌድና ወንፊት እያለ በእጃችን ያልተነፋ ዱቄት ምነው ማቡካታችን
- እርቦ የሆነች አለም ሁሉም የቻለውን ይዘግንባታል



1 2 3 4 5 6 7 8 9 10 11 12

ሴቶችና ሰብአዊ ልማት በኢትዮጵያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች መስፋፋት ጋር በተያያዘ ኢንዱስትሪ እንደ አንድ የኢኮኖሚ ዘርፍ አስተዋጽኦ እያደረገ መምጣቱን እንረዳለን። የኢንዱስትሪ መስፋፋት በተለይ ከሴቶች ሁለንተናዊ ህልውና ጋር የሚያያዝበት ሁኔታም ይስተዋላል። በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ መስፋፋት አካታች እድገትን፣ የሰብአዊ ልማት እድገትን፣ የሰብአዊ መብት መከበርንና የደህንነት መንገድን እንዲያመጣ ይጠበቃል።

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ሲታሰብ የሴቶች ተሳትፎና አመራር ከግምት ውስጥ መግባት አለበት። በሀገራችን የኢንዱስትሪ ፓርክና ሌሎች ኢንደስትራላይዜሽን ሲታሰብ ሴቶች ከጅምሩ እስከ አፈጻጸሙ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል። ከዚያም በላይ ግን ሴቶች በትምህርት ዝግጅታቸው፣ በስራ ልምዳቸውና በብቃታቸው መሰረት በኢንዱስትሪው ልማት ውስጥ የአመራር ቦታ ሊያገኙ ይገባል።

የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እ.ኤ.አ የ2018 የኢትዮጵያ የሰብአዊ ልማት ሪፖርት እንደሚያመለክተው የሀገራት የሰብአዊ ልማት እድገት የሚመጣው በሁሉም መስክ የሴቶች የጾታ እኩልነት ሲረጋገጥና ሴቶች በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካውና በማህበራዊው ዘርፍ እንዲበቁ በማስቻል ነው። ይኸው ሪፖርት አያይዞም ኢንደስትራላይዜሽን የሴቶችን ሰብአዊ ልማት በማሻሻል ረገድ የላቀ አስተዋጽኦ እንዳለው ያመለክታል።

የኢንዱስትሪ ልማትና የሴቶች እኩልነት መብት ተያያዥነት እንዳላቸው ሪፖርቱ አመልክቶ ሴቶች ከወንዶች እኩል በሙያቸው በኢንዱስትሪ ውስጥ ተቀጥረው ሲሰሩና ባላቸው ብቃት የአመራር ቦታ ሲይዙ እኩልነታቸው በቀጥታ ይረጋገጣል። የኢንዱስትሪ ልማት የሴቶችን የእኩልነት መብት የሚያረጋግጠውና የሰብአዊ ልማትን እውን የሚያደርገው የኢንዱስትሪ ልማት ከእቅድ እስከ አፈጻጸም ባለው ሂደት ለስርአተ ጾታ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ፣ ሴቶችንና ልጃገረዶችን ተጠቃሚ የሚያደርግና ለጾታ እኩልነት እንቅፋት የሆኑ አሰራሮችን ሁሉ የሚያስወግድ ብቻ ከሆነ ነው።

ይኸው የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እ.ኤ.አ. የ2018 የኢትዮጵያ የሰብአዊ ልማት ሪፖርት ስለኢትዮጵያ ሴቶች አሳሳቢ መረጃዎችን ይፋ አድርጓል። በዚህም መሰረት፡-

- እድሜያቸው 10ና ከዚያ በላይ ከሆኑት ኢትዮጵያውያን መካከል 32 በመቶ ወንዶችና 51 በመቶ ሴቶች ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ናቸው።
- ከህዝባችን ውስጥ 1.8 በመቶ ብቻ ናቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት።
- የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚጠቀሙ ያገቡ ሴቶች እ.ኤ.አ በ2000 ከነበረበት 6 በመቶ እ.ኤ.አ በ2016 ወደ 35 በመቶ አድጓል። (ይህም ከሰሀራ በታች ካሉ ሀገራት ክፍለ አህጉራዊ አማካይ በመጠኑ ከፍ ያለ ነው)።
- ይህ የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም እድገት በክልሎች መካከል ከፍተኛ ልዩነት ያለው ሲሆን በሶማሌ ክልል እድሚያቸው ከ15-49 ከሆኑ ያገቡ ሴቶች ውስጥ የወሊድ መከላከያ የሚጠቀሙት አንድ በመቶ ብቻ ሲሆኑ በአፋር ክልል ደግሞ ተጠቃሚዎቹ 12 በመቶ ናቸው።
- በሀገራችን የሴቶች ስራአጥ ቁጥር ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር ሶስት እጥፍ ይሆናል።
- የሀገራችን ሴቶች አመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ 1161 ዶላር ሲሆን የወንዶች የነፍስ ወከፍ ገቢ ግን 1886 ዶላር ነው (እ.ኤ.አ በ2016 የመግዛት አቅም መሰረት)።

በሪፖርቱ መሰረት በሀገራችን በሰብአዊ ልማት ዘርፍ ለተገኘው መሻሻል በጤናው ዘርፍ የተገኘው መሻሻል ማለትም የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መሻሻል፣ የህጻናትና የእናቶች ክትባት፣ የጤና ተቋማት ተደራሽነት መሻሻል በህይወት የመኖር እድሜን ከመጨመሩም በላይ አጠቃላዩን ሰብአዊ ልማት እንዲሻሻል አግዟል።

ኢትዮጵያ እንድትለማ የሰብአዊ ልማት ወሳኝ ነው። በተለይ የሴቶች የሰብአዊ ልማት ለሁለንተናዊ የማህበረሰብ ልማት ቁልፍ ነው። ከዚያ በተረፈ ሀገራችን የሁለት አህዝ እድገት አስመዘገበች የሚለው የአጠቃላይ ዓመታዊ ምርት እድገት በእያንዳንዱ ዜጋ ይበልጥ ደግሞ በእያንዳንዷ ሴት ህይወት ውስጥ የሚታይ ለውጥ አያመጣም።

በአለም የኢኮኖሚ ፎረም ላይ ስለሴቶችና ልማት ምን ይሰማል?

በቀኝ የሚታየው በአለም ኢኮኖሚ ትልቅ ድርሻ ያላቸው የአለም መሪዎች በአለም ኢኮኖሚ ፎረም ወቅት በተገናኙበት ወቅት የተሰራ ካርቱን ነው። ካርቱኑ ብዙ ይናገራል። እነዚህ መሪዎች በአንድ ገጹ ድህነትን ስለመዋጋት ሲሰብኩ በሌላ በኩል ደግሞ የህይወትን ኢፍትሀዊነት ያቀጣጥላሉ።

እነዚህ ሀያላን መሪዎች በሚታደሙበት የአለም የኢኮኖሚ ፎረምም የተመረጡ የድሀ ሀገሮች መሪዎችና አንዳንድ ታዋቂ ግለሰቦች የመናገር እድል ይሰጣቸዋል። እስቲ ከባለፈው የኢኮኖሚ ፎረም አንዳንድ ግለሰቦች ስለሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ልማት ያሉትን አባባል እንጥቀስ፡-

- *“ዓለም እየተመራች ያለችው በወንዶች ነው በትክክል እየሄደች እንደሆነ ግን እርግጠኛ አይደለሁም” ሻርሊ ሳንድ በርግ* (Chief Operating Officer of Facebook) *የሴቶች እኩልነት በተመለከተ ያለችው*
- *“የሰው ልጅ ታሪክ እንደሚነግረን ከሆነ መፍራት ያለብን ያጋጠሙንን ችግሮች ሳይሆን ችግሮቻችንን አውቀን መፍትሄ የጠፋብን ዕለት ነው” የቻይና ፕሬዝደንት ሺ ጂንፒን*
- *“አንዲት ሀገር ግማሽ ህዝቦቸዋን ወደኋላ አስቀርታ ትክክለኛ እድገት ማደግ አትችልም።” ጀስቲን ግሪኒንግ* (UK Development of Secretary)
- *“አካል ጉዳተኝነት የስኬት እንቅፋት አይደለም።” ስተፈን ሃውኪንግ* (founder center for theoretical cosmology Cambridge university)
- *“እድገት ማለት ከገንዘብ፣ ማሽን ወይም ፖሊሲ በላይ ስለ ሰው ልጅ ኑሮ የሚመለከት ነው።” ፖል ካጋሚ የሩዋንዳ ፕሬዝደንት*

ጎልማሳ ሊስትሮዎች

ሀይሉ አሰፋ

በቀድሞ ጊዜ ጫማ የሚጠርጉ ሊስትሮዎች በአሰራዎቹ እድሜ የሚገኙ ታዳጊዎች ነበሩ። አሁንስ? አሁንማ እድሜያቸው አርባዎቹን የዘለለ ጎልማሳ ሊስትሮዎችን በከተማችን የተለያዩ ስፍራዎች ማየት የተለመደ ትዕይንት ሆኗል። እንዴት እነዚህ ጎልማሳ ሊስትሮዎች ሊበራከቱ ቻሉ? ሌላ የሚሰራ ስራ አጥተው ነው በአርባና ሀምሳ አመታቸው እንደ ህጻን ድንጋይ ላይ ቁጢጥ ብለው የሰው ጫማ የሚጠርጉት?

ኢኮኖሚው ምን ያህል ቢዳከም ነው እነዚህ በታታሪነታቸው የሚታወቁት የደቡብ ኢትዮጵያ ልጆች በህጻንነታቸው የጀመሩትን ሊስትሮነት የልጅ ልጅ እስኪያዩ የሚሰሩት? መቼም የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት በአንክሮ ስናጤነው በርካታ ጉዳዮች ተሳክረው ይታዩናል። ከዚህ ቀደም የተበጫጨቀ ልብስ የሚለብሱ የጎዳና ልጆች የሚራኮቱበት ትርፍራፊ ምግብ (ቡሌ) በአሁኑ ጊዜ ጸዳ ያለ ልብስ የለበሱ ወጣቶች ከመንገድ ዳር ክብ ሰርተው በስነስርዓት የሚመገቡት መደበኛ ምግብ ሆኗል።

ሃያ ኪሎ የማይመዝን እቃ ከመኪና ላይ ለማውረድ የሚሰበሰበው የወጣት ብዛት የንብ መንጋ ይመስላል። በሰፈር ውስጥ በሀዘንም ሆነ በደስታ ትንሽ ድግስ የተዘጋጀ እንደሆን የድንኳን ሰባሪው፣ የቀላዋጩና የለማኙ ብዛት ድግስ መደገስን እርም የሚያሰኝ ነው።

በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ መሀል የጎልማሶቹ ሊስትሮ ጠራጊዎቹ ሰርተው መብላት እዬዬም ሲደላ ነው የሚለውን ተረት ያስተርት ይሆናል። ግን አንድ ነገር መዘንጋት እንደሌለብንም ያመለክተናል። ከዚህ ቀደም የሊስትሮን ስራ የሚያከናውኑት ህጻናትና ታዳጊ ወጣቶች ነበሩ። እነዚህ ታዳጊ ወጣቶች ለሁለት ሶስት አመታት ከሰሩ በኋላ ወደ ሱቅ በደረቴነት፣ ቀጥሎም የመደብር ባለቤት በመጨረሻም የሱቅ ባለቤት ሆነው ደንበኛ ነጋዴ ይሆኑ ነበር። ወይም ከሊስትሮነት ወደ ሌላ ቢዝነስ ይሸጋገሩ ነበር።

የአሁኖቹ ሊስትሮዎች እስከ ጎልማሳነታቸው በሊስትሮነት መዝለቃቸው ግን የኢኮኖሚውን መታመም በመጠኑም ቢሆን ያመለክታል። ለዚህ ማሳያ የሚሆነንን የአንድ ጎልማሳ ሊስትሮ ግለ ታሪክን እንይ። ጀማል ሻፊ የአርባ አመት ጎልማሳ ሲሆን ከደቡብ ክልል መጥቶ በስድስት ኪሎ አካባቢ ጫማ በመጥረግ የሚተዳደር ሰው ነው። የጀማልን ታሪክ ከራሱ አንደበት እንስማ፡-

< < ከጉራጌ ዞን በ15 አመቴ ወደ አዲስ አበባ ከመጣሁ አሁን ሃያ አምስት አመት ሞልቶኛል። ስራውን ያለማመደኝ በአምስት አመት የሚበልጠኝ ታላቅ ወንድሜ ሲሆን ስራውን ለኔ ትቶልኝ በሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ ተቀጠረ። ከዚያም የራሱን ትንሽ ሱቅ ከፈተ። እኔም የወንድሜን አርአያነት ተከትዬ የጫማ ጠረጋ ስራዬን በርትቼ ያዝኩት። ሶስት አመት ያህል ጠንክሬ ገንዘብ ካጠራቀምኩ በኋላ የልባሽ ጨርቅ (ሰልባጅ) ንግድ ጀመርኩ። ጥቂት ወራት ሰርቼ ስራውን ስለማመድ አንድ ቀን ከመንገድ ዳር በህገ ወጥ ነጋዴነት ስም ዘርግቼ የምሸጠው ሰልባጅ ሁሉ ተወረሰ።

ወንድሜን መነገጃ ገንዘብ ስጠኝ እንዳልለው እሱም እራሱ በሁለት እግሩ ለመቆም እየታገለ ነበር። በቃ ወደ ሊስትሮ ስራዬ ተመለስኩ። አሁንም አንድ አራት አመት ያህል አንጀቴን አስሬ ሊስትሮ ከሰራሁ በኋላ ከአንድ ከማውቀው ሰው አጥር ጥግ በፕላስቲክ ከለላ ሰርቼ አትክልትና ፍራፍሬ መነገድ ጀመርኩ። አሁን ስራው ተሳካልኝ፤ ደንበኞችም አፈራሁ። ገበያ ለመሳብ ስል ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ጥቅል ጎመን፣ ካሮትና የመሳሰሉትን ከሌሎች እየቀነስኩ እሸጥ ስለነበር በአጭር ጊዜ ውስጥ ገበያዬ ደራ። ታዲያ ምን ያደርጋል ምቀኛ ተነሳብኝ።

አንድ ቀን በምቀኞች መሪነት ደንብ አስከባሪዎች መጡና የላስቲክ መደብሬን አሸጉብኝ። < <ከአሁን በኋላ ንግድ ፈቃድ ሳታወጣ ብትሰራ ትታሰራለህ> > ብለው ዛቱብኝ። እኔም ንግድ ፈቃድ በአንድ ቀን የሚወጣ መስሎኝ ቀበሌ ብሄድ፣ አንዴ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪነትህን የሚያረጋግጥ መታወቂያ፣ አንዴ ጉዳዩ የሚመለከተው ክፍለ ከተማውን ነው፣ አንዴ ከአነስተኛና ጥቃቅን የድጋፍ ደብዳቤ አምጣ እያሉኝ ከሳምንት በላይ አጉላሉኝ። በዚህ መሀል ለሽያጭ ያቀረብኩት አንድ ፒካፕ መኪና አትክልትና ፍራፍሬ ከጥቅም ውጪ ሆነ።

ከዚህ በኋላ ሁሉ ነገር ጠመመብኝ። የቀረችኝን ትንሽ ጥሪት አሰባስቤ የተለያዩ አነስተኛ ንግዶችን ብጀምርም አልሳካ አለኝ። መቼስ ምን ይደረጋል አላህ አላለውም። በጉራጌ ባህል ልመናም ሆነ የሰው እጅ ማየት ነውር ነውና ሰርቼ ለመብላት ስል በሀያ ምናምን አመቴ ዳግም ወደ ሊስትሮነት ተመለስኩ። ከዚህም በኋላ ከሊስትሮነት ለመውጣት ብዙ ጊዜ ጥሬ ነበር እየተመለስኩ የምወድቀው ግን ያው ጫማ ጠረጋ ላይ ነው።

የሚገርመው ግን ይህ ታሪክ የኔ ብቻ አይደለም። እንደኔው ከሊስትሮነት ለመውጣት ታግለው ያልተሳካላቸውና አርባ ሀምሳ አመት የሞላቸው ጓደኞቼ ብዙ ናቸው። ምን ታደርገዋለህ አላህ አልፈቀደልንም> > ሲል ጀማል ሻፊ ህይወቱን ይተርካል።

ግን ጀማል እንዳለው አላህ ስላልፈቀደ ብቻ ነው ወይስ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የአስተዳደር ስርዓታችን እንደ ጀማል ያሉትን ጥረው ግረው የሚበሉ ዜጎችን የማይደግፍ በመሆኑ ነው?

እኔ እወድሻለሁ

ከብዙ ቀስማለች ሰፊ ነው ትምህርቷ
እንዴት ያምርባታል ቀለም ባንደበቷ።

ገብረ ክርስቶስ ደስታ

ብዙ ሺ ዘመናት
　　　　እልፍ አእላፍ ሌሊት፤
ሚሊዮን መሰለኝ
ፍቅሬ አንቺን ስወድሽ ቀኑ ረዘመብኝ።
　　　　እኔ እወድሻለሁ
የሰማይ መሬቱን፤
የባህር ስፋቱን
እንዳለም ዳርቻ የርቀቱን ያህል።
　　　　እንደ ጽጌረዳ
　　　　እንደ አደይ አበባ፤
　　　　እንደ ሎሚ ሽታ፤
እንደ ከርቤ ብርጉድ ፤ እንደጣን ጪስ እንጨት
ውድ እወድሻለሁ
አበባ እንዳየ ንብ፤
እንደ ቢራቢሮ ጫካ እንደሚያስሰው
ፍቅርሽን በፍቅሬ በፍቅርሽ ልቅመሰው።
ማር ወለላዬ ነሽ ከረሜላ ስኳር
አማርኛ አይበቃ
　　　　（ወይ ጉድ ! ）
ባለም ቋንቋ ሁሉ ቢወራ ቢነገር።
　　　　እኔ እወድሻለሁ።
እንደማታ ጀንበር፤
እንደ ጨረቃ ጌጥ፤
እንደ ተወርዋሪ ኮኮብ የማልጠግብሽ
　　　　ስወድሽ፤ ስወድሽ፤
　　　　ስወድሽ፤ ስወድሽ።
ጡት እንዳየ ህጻን ወተት እንዳማረው
ጠጋ በይ ዘመዴ አፍሽ ህይወቴ ነው።
ጣይ ላይ ያ ቅቤ ....
ገላዬ ገላሽን ሲነካ የሚያልቀው
አፈር መሬት ትቢያ ውሀ እንደሚበላው
ፍቅሬ አንቺን ስወድሽ ....
　　　　ብዙ ሺ ዘመናት
　　　　እልፍ አእላፍ ሌሊት፤
ውድ እወድሻለሁ።
አይኖችሽን ባይኔ ተዳክሜ እያየሁ።
ስወድሽ፤ ስወድሽ፤
　　　　ውድ እወድሻለሁ።

ገብረ ክርስቶስ ደስታ

ተስፋና ስጋት የወጣቷ ህይወት

የህንስ ታሪኩ

የርዳኖስ ተሾመ የ24 ዓመት ወጣት ስትሆን በ2011 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከቴአትር ጥበባት ክፍል በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቃለች። በአሁኑ ወቅት ቋሚ ስራ ባይኖራትም በሙያዋ የተለያዩ ጊዚያዊ ስራ እየሰራች አዲስ አበባ ውስጥ ከጓደኞቿ ጋር ቤት ተከራይታ ትኖራለች። የየርዳኖስ ህይወት በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ያለችን የአንዲት ከዩኒቨርስቲ የተመረቀች ወጣት ሴትን ህይወት በተምሳሌትነት እንድናይ ያስችለናልና ቃለምልልሱን እንድተከታተሉ እንጋብዛለን፦

መላ ምቺ - እስቲ ስለራስሽ ንገሪን?

የርዳኖስ - የርዳኖስ ተሾመ እባላለሁ። ተወልጄ ያደኩት ሶማሌ ክልል ጂግጂጋ ከተማ ውስጥ ነው። ከልጅነቴ ጀምሮ የኪነጥበብ ፍቅር ስለነበረኝ ዩኒቨርስቲ ስገባ ቴያትር ጥበባት ዲፓርትመንት የገባሁት በምርጫዬ ነው። እራሴን ለኪነጥበብ እንደተፈጠረ ሰው ነው የምቆጥረው።

መላ ምቺ - በቴያትር ዲፓርትመንት ውስጥ በቂ እውቀት ገብይቻለሁ ብለሽ ታምኚያለሽ?

የርዳኖስ - አላምንም

መላ ምቺ - ለምን?

የርዳኖስ - አገኛለሁ ብዬ የጠበኩትን ያህል እውቀት አላገኘሁማ! አንዳንዱ መምህር ያሾፋል። አንዳንዱ መምህር ምንም ሳይሰጥህ አሳይመንት ብቻ እያሰራህ ጊዜህን ያባክናል። በርግጥ ጥሩ ጥሩ መምህራንም አሉ። ብቻ የጠበኩትን ያህል ዕውቀት አላገኘሁም ብል ሁኔታውን ይገልጸዋል።

መላ ምቺ - እሺ አሁን ከተመረቅሽ በኋላ ምን እየሰራሽ ነው?

የርዳኖስ - ከተፋ

መላ ምቺ - ከተፋ ደግሞ ምንድነው?

የርዳኖስ - ከተፋ ማለት ጊዜያዊ ስራ ነው። እንደተገኘ የማስታወቂያ ስራ፣ አጫጭር ድራማዎችንና የዶክሜንተሪ ስራዎችን እሰራለሁ።

መላ ምቺ - ለዚህ ስራ ምን ያህል ይከፈልሻል?

የርዳኖስ - አንድ ሰዓት ያህል ለሚፈጅ ቀረጻ ከ1,200 እስከ 2,000 ብር ይከፈለኛል። እንዲህ አይነት ተባራሪ ስራ በወር ሁለት ወይም ሶስት ይገኛል።

መላ ምቺ - ቋሚ ስራ ማግኘት አልቻልሽም?

የርዳኖስ - በርግጥ እስካሁን ቋሚ ስራ አላገኘሁም። ግን ቋሚ ስራ ባገኝም እንደኔ ያለች ዜሮ ዓመት የስራ ልምድ ያላት ከ3,500 ብር በላይ አትቀጠርም። ይቺንም ስራ ለማግኘት በተለማማጅ ሰራተኝነት በነጻ ማገልገል ይጠይቃል። ስለዚህ ለጊዜው ከተፋው ሳይሻል አይቀርም።

መላ ምቺ - እንዳንቺ ላለች ቋሚ ስራ ለሌላት ወጣት ተመራቂ ኑሮ በአዲስ አበባ ምን ይመስላል?

የርዳኖስ - ከባድ ነው። ብዙ ፈተናዎች አሉ። ስራ ለማግኘት ፈተና ነው። አንዳንዱ ከሙያዬ በፊት ሰውነቴን እንድሸጥለት ይፈልጋል። የሆነ የኪነጥበብ ስራ ሊያሰራኝ የፈለገ የፊልም ዳይሬክተር ወይም ፕሮዲዩሰር ደውሎ <<ስራ አገኝቼልሻለሁ። ማታ እራት እየበላን ብንወያይስ?>> ይላል። እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ችግሩ።

መላ ምቺ - እራቱ ጣጣ ይዞ ይመጣል ማለትሽ ነው?

የርዳኖስ - አንድ ጣጣ ብቻ?! ለምን አንድ ገጠመኜን አላጫውትህም። አንድ ጊዜ በጣም የማውቀውና የምግባባው የፊልም ዳይሬክተር በፊልሜ ላይ እንድትተውኝልኝ እፈልጋለሁና የፊልም ስቱዲዮ ውስጥ እንገናኝ አለኝ። እኔም እንኳን ማታ እራት ላይ እንገናኝ አላለኝ ብዬ ከስቱዲዮው ከች አልኩኝ። ከዚያ ፊልሙ ተረሳና ሌላ ወሬ ጀመረ። ሙዱ ሁሉ ተቀየረ። በል በል አቁም አልኩት። እንዲህማ ግግም ብለሽ ጭራሽ የፊልም ስራ አታገኚም አለኝ። ሺ ጊዜ አላገኝ እንጂ ገላዬን አልሸጥም ብዬው ተቆራረጥን።

መላ ምቺ - ዳይሬክተሩ እንዳለው ከዚያ በኋላ ጭራሽ የፊልም ትወና ስራ አላገኘሽም?

የርዳኖስ - እሱ እንዳለው ባይሆንም ፈተናው ቀላል አይደለም። ከዚህ ገጠመኝ በኋላ በርካታ ችሎታና ተሰጥኦ የሌላቸው ሴቶች ለአሰሪዎቻቸው የወሲብ ጥያቄ ፈቃደኛ እየሆኑ የፊልምና የማስታወቂያ ስራ ሲያገኙ አይቻለሁ። እኔ እንቢ ያልኩትን ሌላኛዋ እህቴ እሺ ስትል በጣም ያናድደኛል።

መላ ምቺ - እዚህ ላይ ግን ወንዱን ብቻ ተጠያቂ ማድረግ አለብን?

ዮርዳኖስ - እርግጥ ነው ከሴቷ < < አይሆንም> > የማለት ጽናት ይጠበቃል። በሌላ በኩል ደግሞ አጣብቂኝ ውስጥ የሚከት ሁኔታ አለ። እስቲ ልብ ብለን እንይ! አንዲት ወጣት ተማሪ ወይም ተመርቃ ስራ ያጣች ወጣት፣ ወደፊት በሙያዋ ታዋቂ ለመሆን ህልም ያላት፣ በዚያ ላይ የሚረዳት የሌላት፣ ይብሱኑ ደግሞ የዕለት ጉርስ የሌላት ስራና ገንዘብ ለማግኘት ስትል ያለፍላጎቷ ወሲብ ብትፈጽም በሁኔታው ተገዳ እንደሆነ እንረዳለን።

መላ ምቹ - አንቺ ግን ይህን ሁሉ ወሲባዊ ሁከት እንዴት ተቋቋምሺው?

ዮርዳኖስ - እኔ እራሴን እንደተለየች ሴት አላይም። ከጂግጂጋ የመጣሁትም ለኪነጥበብ ስል ነው። እራሴን ለኪነጥበብ እንደተፈጠረ ሰው ነው የምቆጥረው። እኔ ወደፊትም ሌላ ስራ አልሰራም ከኪነጥበብ ውጪ። ስለዚህ በሙያዬና በችሎታዬ ብቻ ተጠቅሜ ነው ገንዘብ ማግኘት የምፈልገው።

መላ ምቹ - እንዲያው አንዳንዴ ሌሎች ሴቶች ያደረጉትን እኔስ ባደርገው የሚል ሀሳብ ወደ ህሊናሽ አይመጣም?

ዮርዳኖስ - < < ለኔ ያለው የትም አይሄድም> > የሚል እምነት አለኝ። ወይም ደግሞ አንድ ስራ በወሲብ ጥያቄ ምክንያት ቢደናቀፍብኝ < < ለኔ ባይለው ነው> > ብዬ እጽናናለሁ። ደግሞኮ በጣም የሚያስገርመውና የሚያሳዝነው አንዳንድ ሴቶች ስራውን አገኘዋለሁ ብለው ወሲብ ከፈጸሙ በኋላ ስራውን የማያገኙበትም ሁኔታ አለኮ! ወይም ደግሞ ገላዋን አርክሳ እዚህ ግባ የማይባል ትንሽ ስራና ትንሽ ገንዘብ የምታገኝም አለች።

መላ ምቹ - ሴት ተዋንያን ሰብዓዊ መብታቸው ተጠብቆ በሙያቸውና በችሎታቸው ብቻ ተመዝነው እንዲሰሩ ምን መደረግ አለበት ትያለሽ?

ዮርዳኖስ - የካስቲንግ ኤጀንት አሰራር ተግባራዊ መደረግ አለበት።

መላ ምቹ - ካስቲንግ ኤጀንት ምንድነው?

ዮርዳኖስ - ካስቲንግ ኤጀንት ማለት ህጋዊ እውቅና ያለው ተቋም ሆኖ ለአንድ ፊልም፣ ማስታወቂያ ወይም ድራማ ተዋንያንን በችሎታቸውና በተስጥኦዋቸው ብቻ መዝኖ የሚመለምል ድርጅት ነው። ድርጅቱ ማስታወቂያ ያወጣል፤ በማስታወቂያው መሰረት ለስራው እንመጥናለን የሚሉ ተዋንያን መረጃቸውን አያይዘው በኢሜል ወይም በአካል ያመለክታሉ፤ ለስራው ብቁ የሆኑት ይመረጣሉ። በዚህ አሰራር ማንም ታዋቂ ነኝ የሚል ዳይሬክተርና ገንዘብ አለኝ ባይ ፕሮዲዩሰር የሴት ተዋንያንን ቅርጽና ውበት እየመዘነ የወሲብ ጥያቄ የሚያቀርብበት ሁኔታ ይቀንሳል።

መላ ምቹ - ይሄስ አሰራር ችግሩን ያስወግደዋል?

ዮርዳኖስ - ያስወግደዋል አላልኩም። ይቀንሰዋል ነው ያልኩት።

መላ ምቹ - በኪነጥበቡ አለም ወሲባዊ ትንኮሳና ጥቃት ይህን ያህል ስር የሰደደ ችግር ነው?

ዮርዳኖስ - ካላለባበስነው በስተቀር ስር የሰደደ ችግር ነው። ግን ደግሞ ሙያው ከሚፈጥረው መቀራረብና ነጻነት አንጻር ችግሩ ባደጉትም ሀገራት ያለ ይመስለኛል። ስለዚህ ችግሩ የነበረ፣ ያለና ወደፊትም የሚኖር መሆኑን በመገንዘብ በሴቶች ዘንድ < < ኖ! አይሆንም! > > የማለት ጽናት ሊኖር ይገባል።

መላ ምቹ - ሁሉም ሴቶች < < ኖ! አይሆንም! > > ማለት ይችላሉ?

ዮርዳኖስ - እንዴት መሰለህ፤ በርግጥ ልምድ የሌላቸው ሴቶች በመጀመሪያ ወቅት ሊታለሉ ይችላሉ። አሰሪው ወንድ እራት እንብላ ሲላት ለመጀመሪያ ጊዜ ጉዳዩ እራት በመብላት ብቻ የሚያልቅ ይመስላታል። ስለዚህ ልምድ ያላት ሴት በእድሜ አነስ ላለችውና ልምድ ለሌላት ሴት ተዋናይ የመምከርና የማስጠንቀቅ ኃላፊነት አለባት።

መላ ምቹ - አንቺ አድርገሽዋል?

ዮርዳኖስ - በሚገባ! እኔ አሁን ማታ እራት እየበላን ስለስራ እናውራ የሚለኝ ፊልምና ማስታወቂያ አሰሪ ዘንድ አልሄድም። ሌላው ይቅርና በቀን ሲጠራኝ እንኳ የሴት ጓደኛዬን ይዤ ነው የምሄደው። ከኔ ሙያዬን ብቻ የሚፈልግ ሰው ለምን ማታ አልመጣሽም ወይም ለምን ጓደኛሽን ይዘሽ መጣሽ ብሎ ስራ አይከለክለኝም። እና ይህን ልምዴን ለበርካታ በእድሜና በልምድ ከኔ ለሚያንሱ የኪነጥበብ ተማሪዎች እያካፈልኩ እገኛለሁ።

መላ ምቹ - በዚህ ጥረትሽ ምን ያህል ውጤታማ ነሽ ?

ዮርዳኖስ - አንዲት ወጣትም ማዳን እኮ ትልቅ ነገር ነው።

መላ ምቹ - እስቲ አሁን ደግሞ ወደ ሌላ ርእሰ - ጉዳይ እንሸጋገርና የሰሞኑን የዩኒቨርስቲዎችን ብጥብጥ እንዴት ታይዋለሽ? አንቺ ራስሽ ባለፈው አመት መጨረሻ ላይ ከዩኒቨርስቲ ስለተመረቅሽ ለዩኒቨርስቲ ህይወት ቅርብ ነሽ።

ዮርዳኖስ - እርግጥ ነው። አሁንም በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የሚማሩ ጓደኞች አሉኝ። እኔ ራሴ ዩኒቨርስቲ በነበርኩበት ወቅት በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ሰላም አልነበረም። የሰሞኑ የዩኒቨርስቲዎች ረብሻ ግን የባሰ ነው።

መላ ምቹ - ከሌላው ጊዜ ይብሳል ?

ዮርዳኖስ - በኔ አስተሳሰብ ይብሳል ባይ ነኝ። ተማሪዎች ተገድለዋል፤ ከካምፓስ ውጪ በቤተክርስቲያን ተጠልለዋል፤ በርካታ ተማሪዎች የመኝታ ክፍላቸው ለደህንነታቸው ስጋት ስለሆነባቸው በአዳራሾች ውስጥ በቡድን ለመተኛት ተገደዋል፤ አንዳንዶችም ከዩኒቨርስቲ ግቢ ወጥተው አስተማማኝ ባልሆነ ሁኔታ በየሰዉ ቤትና በየቤርጎው ለማደር ተገደዋል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ከቤተሰቦቿ ተለይታ ለማታውቅ ጀማሪ የዩኒቨርስቲ ተማሪ እንዲሁም ለሴት ተማሪዎች ባጠቃላይ ከባድ ፈተና ነው።

መላ ምቹ - ለሴት ተማሪዎች ፈተና ነው ስትይ ምን ማለትሽ ነው? አስቲ ትንሽ ዘርዘር አድርገሽ ግለጪው።

ዮርዳኖስ - ሰሞኑን የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ሲረበሽ እዛው ድሬዳዋ ነበርኩ። ድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የምትማር ጓደኛ አለችኝ። እሷም እንደኔ የጂግጂጋ ልጅ ነች። ዩኒቨርስቲው ውስጥ ማደር ስላልቻለች እንደምንም ከጊቢው ወጣች። ግን ማደሪያ አልነበራትም። በስልክ ተደዋውለን እኔ አልጋ ወደ ያዝኩበት ሆቴል እንድትመጣ አደረኩ። በሆቴል ውስጥ 350 ብር እየከፈልን ሁለት ቀን ከኔ ጋር ካደረች በኋላ ትራንስፖርት መንቀሳቀስ ሲጀምር ወደ ቤተሰቦቿ ጂግጂጋ ሄደች።

መላ ምቹ - ምንም ጉዳት ሳይደርስባት ከቤተሰቦቿ ጋር ተቀላቀለች ማለት ነው።

ዮርዳኖስ - ግን እንዳጋጣሚ እኔን ባታገኝስ የት ታድር ነበር? ገንዘብ ቢኖራት እንኳ ለወጣት ልጃገረድ ብቻዋን ቤርጎ ማደር ያሰጋል። በዚያ ላይ ብቸኝነቷን ያየ አንዳንድ ስነምግባር የሌለው ወንድ ወሲባዊ ጥቃት ሊፈጽምባት ይችላል። አንዳንዱ አፈ ቂቤ ወንድ ግራ መጋባቷንና መሸበሯን ያየ <<ነይ ከቤተሰቦቼ ጋር ታድሪያለሽ>> ብሎ ጉድ ሊያደርጋት ይችላል። ኧረ በረብሻ ሰዓት የሚፈጠር ስንት ጉድ አለ!

መላ ምቹ - ለማሳረጊያ አንድ ጉዳይ ላንሳ። የወቅቱ የሀገራችን ፖለቲካ ሁኔታ እንዳንቺ ባለች ወጣት ተመራቂ እይታ ሲቃኝ ምን ይመስላል?

ዮርዳኖስ - (ትንሽ ተከዝ ብላ ቆየችና) እኔ በፖለቲካና በሀይማኖት ጉዳይ ላይ መነጋገር አልፈልግም። ግን የወቅቱ የሀገራችን ሁኔታ ሁሉንም ሰው ፖለቲከኛ አድርጎታል። እኔ መጪውን ጊዜ የማየው በስጋት ነው። ደግሞም የፖለቲካ ቀውስና የሰላም እጦትን በአንድ ወቅት በአይኔ በብረቱ ስላየሁ የወደፊቱ ሁኔታ ያሰጋኛል።

መላ ምቹ - ምንድነው በአይንሽ በብረቱ ያየሽው?

ዮርዳኖስ - ሀምሌ 28/2010 ዓ.ም የሶማሌ ክልል ቀውስ ሲቀሰቀስ እዛው ጂግጂጋ ነበርኩ። እንዳጋጣሚ በረብሻው ዋዜማ ከመሀል ከተማ ወጣ ካለው የጓደኛዬ ቤት ነበር ያደርኩት። ምንም የሰማነውና ያየነው ነገር አልነበረም። ከእንቅልፋችን ስንነቃ ከተማዋ ተቀውጣለች። ወደ ቤቴ መሄድ አልቻልኩም። በከተማዋ መንገዶች ላይ ምንም አይነት ተሽከርካሪ አይንቀሳቀስም። መንቀሳቀስ የሚችለው አምቡላንስ ብቻ ነው። በሰዎች እርዳታ በአምቡላንስ እንደምንም እናቴ ቤት ገባሁ።

መላ ምቹ - በረብሻው ወቅት ጂግጂጋ ምን ትመስል ነበር?

ዮርዳኖስ - ጭራሽ አይኔን ማመን ነው ያቃተኝ። በአምቡላንስ ወደ ቤት ስሄድ ኪዳነ-ምህረት ቤተ ክርስቲያን ተቃጥላለች፣ በርካታ ለህይወታቸው የሰጉ የከተማው ነዋሪዎች ሚካኤል ቤተክርስቲያን ተጠልለዋል፣ ሱቆችና መኖሪያ ቤቶች ይቃጠላሉ፣ የተዘረፉ ንብረቶች በየመንገዱ ተበታትነዋል፣ ብቻ ምን ልበልህ ተወልጄ ያደኩበት ከተማ አልመስልሽ አለኝ። እኔ ከዚያ በፊት እንደዚያ አይነት ውድመት ያየሁት ወይ በፊልም ነው ወይም በአረብ ሀገራት ጦርነት ነው።

መላ ምቹ - በብጥብጡ አንቺ የምታውቂያቸው ህይወታቸውን ያጡ ሰዎች አሉ?

ዮርዳኖስ - አሉ እንጂ! ሁለት በደንብ የማውቃቸው የጅግጅጋ ወጣቶች በጥይት ተመተው ሞተዋል። አንዷት በቅርበት የማውቃት ወጣት ልጅ ደግሞ ሚካኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ በጥይት ተመትታ ቆስላለች። እናም ያንን ብጥብጥ ካየሁ በኋላ የሰላምን ዋጋ በእጅጉ ተረዳሁ። ያ ሁኔታ በፍጹም እንዲደገም አልፈልግም።

መላ ምቹ - በመጪው ግንቦት ወር አጠቃላይ ብሔራዊ ምርጫ ይካሄዳል እየተባለ ነው። በምርጫው ምን የሚከሰት ይመስልሻል?

ዮርዳኖስ - ስጋት አለኝ። በአሁኑ ጊዜ በምንም ነገር ላይ መተማመን አይቻልም። ዛሬ ሰላም ነው ያልከው ቦታ ነገ ይረበሻል። ለምሳሌ ሀምሌ 2010 ዓ.ም ሶማሌ ክልል ሲረበሽ ሌላው ስፍራ ሰላም ነበር። ሶማሌ ክልል ሰላም ሲሆን ደግሞ በየተራ ሌላው ስፍራ ሰላም አጣ። ስለዚህ ምንም ነገር ማመን አንችልም። ምርጫውንም ሰላማዊ ይሆናል ብዬ ለማመን እቸገራለሁ።

መላ ምቹ - ታዲያ ምን ቢደረግ ይሻላል?

ዮርዳኖስ - ሀገር በአስተማማኝ ሁኔታ እስኪረጋጋ ምርጫው ቢራዘም እመርጣለሁ። እንደ አንዲት ስራ ፈላጊ ወጣት ምርጫውን በጉጉት እንድጠብቀው የሚያደርገኝ ምንም ነገር የለም። ደግሞ በምርጫ ሰበብ የሰው ልጅ በአሰቃቂ ሁኔታ ይገደል እንዴ?!

መላ ምቹ - በአጠቃላይ መጪውን ጊዜ እንዴት ታይዋለሽ?

ዮርዳኖስ - እንደ አንዲት የዩኒቨርስቲ ተመራቂ ስራ ይዤ የተሻለ ህይወት ለመምራት ተስፋ አደርጋለሁ። በሌላ ጎኑ ደግሞ ስጋት አለኝ። ለማንኛውም እግዚአብሔር ሰላሙን ይስጠን እላለሁ።

መላ ምቹ - አሜን

ዮርዳኖስ ተሾመ

የኩላሊት ነገር

ኩላሊት ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ደም በማጣራት በሰውነታችን ውስጥ የማያስፈልጉ ነገሮችን በሽንት መልክ ማስወገድ አንዱ ነው። በሰውነታችን ውስጥ የተጠራቀመ አላስፈላጊ ውሃን ማስወገድ እና የካልሺየምና የፎስፌት ማዕድናት መጠንን መቆጣጠርም ሌላኛው ስራው ነው። የደም ዝውውርን የሚያፋጥኑና የቀይ ደም ህዋስ መመረት ሂደትን የሚጨምሩ ሆርሞኖችንም ያመርታል።

በርካታ ተግባራት የሚከውነው ኩላሊት ጤናማ ሆኖ እንዲቀጥልና ስራውን በተገቢው መንገድ እንዲያከናውን ታዲያ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ነገሮች መራቅ ይገባል።

1. ሽንትን ይዞ መቆየት

ሽንት ሳይወገድ በፊኛ ለረዥም ጊዜ ከቆየ ለባክቴሪያዎች መፈጠር ምክንያት የሚሆን ሲሆን፥ ይህም የሽንት ወይም የኩላሊት ኢንፌክሽን ይፈጥራል። ስለሆነም በስራ ውጥረትም ይሁን ሌላ የተፈጥሮ ጥያቄን መልስ የሚያዘገዩ ከሆነ ለኩላሊትዎ ሲሉ ከድርጊትዎ ሊቆጠቡ ይገባል እንላለን።

2. በቂ ውሃ አለመጠጣት

ኩላሊት አላስፈላጊ ነገሮችን ለማስወገድ ተግባሩ በቂ ውሃ ስለሚፈልግ በቀን ውስጥ በቂ ውሃ አለመጠጣትም ለኩላሊት ህመም ይዳርጋል። ሰውነታችን አስፈላጊውን ያህል ውሃ ካላገኘ ደም ስለሚረጋ ወደ ኩላሊታችን የሚሄደው ደም መጠን ይቀንሳል። ይህም ኩላሊት ከሰውነታችን የሚያስወግዳቸው መርዘኛ ተህዋሳት በበቂ ሁኔታ እንዳይወገዱ ያሰናክላል ማለት ነው። ስለሆነም በየቀኑ ከ10 እስከ 12 ብርጭቆ ውሃ መጠጣት ኩላሊትዎ ጤናማ እንዲሆን ያግዛል።

3. ጨው አብዝቶ መመገብ

በተደጋጋሚ ጨው የበዛበት ምግብ መመገብም ለኩላሊት ጤና ፀር ነው ተብሏል። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ጨውን አብዝቶ መውሰድ በሽንታችን ውስጥ የፕሮቲን መጠን እንዲጨምር በማድረግ ለኩላሊት ህመም ይዳርጋል። በየቀኑ በአጠቃላይ ከምንወስዳቸው ምግቦች ውስጥ የጨው ድርሻ ከ5 ግራም ባይበልጥ መልካም ነው ይላሉ ባለሙያዎች።

4. መድሃኒቶችን/ ማስታገሻዎችን አዘውትሮ መውሰድ

ብዙዎቻችን ጉንፋን አልያም ራስ ምታት ሲያመን በሽታ የመከላከል አቅማችንን የሚያጎለብቱ ምግቦችና መጠጦችን ከመውሰድ ይልቅ ኪኒን ስለመዋጥ ነው የምናስበው። መድሃኒቶች በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ኩላሊታችንን አልያም ሌላ የሰውነት ክፍላችንን ሊጎዱ እንደሚችሉ ይነገራል። አንዳንድ ጥናቶች ማስታገሻዎችን በተደጋጋሚ መውሰድ ወደ ኩላሊት የሚሄደውን ደም እንቅስቃሴ ሊቀንሱ እንደሚችሉ አመላክተዋል።

5. ፕሮቲን የበዛባቸው ምግቦች

ፕሮቲን ለጤና ጠቃሚ ቢሆንም፥ ቀይ ስጋና የፕሮቲን መጠናቸው እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ምግቦችን በተደጋጋሚ መውሰድ ለኩላሊት በሽታ ሊያጋልጥ ይችላል።

6. አልኮል

የአልኮል መጠጦችን አብዝተን በምንጠጣበት ወቅት ዩሪክ አሲድ በኩላሊታችን ቱቦ ይከማቻል። ይህም ኩላሊታችን የተለመደ ተግባሩን እንዳያከናውን እክል ይፈጥራል። ስለሆነም ሁሉም በልኩ ነውና በመጠጡም ለጤናዎ ይወቁበት።

7. ሲጋራ

ሲጋራ ማጨስ በሁሉም የሰውነታችን ክፍሎች የሚያደርሰው አስከፊ ጉዳት አጠያያቂ ባይሆንም ለኩላሊት ህመም እንደሚያጋልጥም ይነገራል። ሲጋራ እድሜ እየገፋ ሲመጣ ለሚከሰተው የኩላሊት ህመም መንስኤ ከመሆኑም ባሻገር የኩላሊት ህመምተኞች አጫሾች ከሆኑ ደግሞ በሽታው እጅግ እንዲባባስ እንደሚያደርግ በጥናት ተረጋግጧል።

8. ቡና (ካፊይን አብዝቶ መጠቀም)

ካፊይን አብዝቶ መጠቀም ለደም ግፊት ከመዳረጉም ባለፈ ኩላሊትንም ይጎዳል። ካፊይንን ካለልክ መውሰድ ለኩላሊት ጠጠር መፈጠር ምክንያት የሚሆን ሲሆን፥ የካልሺየም ንጥረ ነገር ከሽንት ጋር በብዛት እንዲወገድም ያደርጋል።

9. ጉንፋንን የመሳሰሉ ህመሞችን ቸል ማለት

እንደ ጉንፋን፣ ቶንሲል፣ ኢንፍሎዌንዛ ያሉ ህመሞችን በቸልታ ማለፍ ኩላሊትን ሊጎዱ እንደሚችሉ ይነገራል። እነዚህ ቀላልና የተለመዱ ህመሞችን የሚያመጡ ባክቴሪያዎችና ቫይረሶች አስፈላጊው ህክምና በወቅቱ ካልተደረገ ኩላሊትን የመጉዳት አቅም አላቸው።

10. እንቅልፍ ማጣት

በተጣበበ ጊዜና የስራ ሁኔታ የሚኖሩ ሰዎች እንቅልፍ የሚያስገኘውን የጤና በረከት ይዘነጉታል። በእንቅልፍ ሰዓት አዳዲስ ህዋሳት አሮጌዎቹን የመተካት ተግባር ይከናወናል። በአንፃሩ በቂ እንቅልፍ አለማግኘት እንደ ኩላሊት ያሉ ሌሎች የሰውነት አካላት ተግባራቸውን በተገቢው ሁኔታ እንዳያከናውኑ ያደርጋል። በተጨማሪም በቂ እረፍት ወይም እንቅልፍ አለመኖር ለደም ግፊት ይዳርጋል።



በመጨረሻም የሽንት ቀለም መቀየር፣ ማስመለስ፣ የአተነፋፈስ መዛባት፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ ድካም እና የመሳሰሉት የኩላሊት በሽታ ምልክቶች ሊሆኑ ስለሚችሉ በአፋጣኝ ወደ ህክምና ተቋማት መሄድ ይመከራል።

የተረሳ ጣጣ

አሰፋ ሀይሉ

በሀገራችን ከአስር ዓመታት በፊት ህዝብንም መንግስትንም በእጅጉ እንቅልፍ የነሳ አንድ ጉዳይ ነበር - ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ። ይህን ችግር አገር ተረባርቦ እንዳስታገሰው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ከዚያስ? ከዚያማ ችግሩን ድል መተነዋል ብለን ችላ አልነው። እንዲያውም ጭራሱኑ ተዘናጋን ማለት ይቻላል። አጅሬ መዘናጋታችንን አይቶ፣ ችላ መባሉን ገምቶ ይኸው እነሆ አድብቶ መጥቶብናል።

ከጤና ተቋማትና ከጤና ባለሙያዎች ይፋ በተደረገው መሰረት በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ አካባቢዎች የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭት 1.3 በመቶ ደርሷል። በዓለም አቀፍ የጤና አጠባበቅ መለኪያ መሰረት የአንድ በሽታ ስርጭት ከነዋሪው ህዝብ 1.3 በመቶና ከዚያ በላይ ከሆነ ወረርሽኝ ደረጃ ደርሷል ይባላል።

ከብሔራዊ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ድርጅትና ከአሜሪካ የበሽታዎች መቆጣጠሪያ ድርጅት ያገኘነውን መረጃ እንደሚከተለው እናቀርባለን።

- የሀገራችን ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭት ከፍተኛው 4.8 በመቶ ጋምቤላ ክልል ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ ሶማሌ ክልል 0.1 በመቶ ነው።
- በሀገሪቱ የኤች.አይ.ቪ. ስርጭት በ2000 እ.ኤ.አ 3.3 በመቶ የነበረ ሲሆን እ.ኤ.አ በ2017 ወደ 0.9 በመቶ ዝቅ ብሎ ነበር።
- እ.ኤ.አ በ2000 ከኤች.አይ.ቪ. ጋር በተያያዘ የሞቱት 83,000 ሰዎች ሲሆኑ በ2017 ደግሞ የሞቱት ሰዎች ቁጥር ወደ 15,600 ዝቅ ብሏል።
- በኢትዮጵያ ከኤች.አይ.ቪ. ጋር ከሚኖሩ ወገኖች ውስጥ 39 በመቶ ወንዶች ሲሆኑ 61 በመቶ ደግሞ ሴቶች ናቸው።
- በ2009 ዓ.ም በኤች.አይ.ቪ. ከተያዙት 27,288 ሰዎች ውስጥ 16,021 (59%) ሴቶች ሲሆኑ 11,267 (41%) ደግሞ ወንዶች ናቸው።
- እ.ኤ.አ በ2016 ከተፈጸሙት ጾታዊ ጥቃቶች ውስጥ 7 በመቶ ወሲባዊ ጥቃቶች ናቸው።
- እ.ኤ.አ በ2017 በአንድ ዓመት ውስጥ በጋንዲ ሆስፒታል ከወለዱ 111 እናቶች መካከል 31 የሚሆኑት በኤች.አይ.ቪ. የተያዙ ሆነው ተገኝተዋል።
- የመደፈር ጥቃት ተፈጽሞባቸው መጥተው በዚሁ ሆስፒታል ህክምና ከተደረገላቸው 21 ሴቶች መካከል ዘጠኙ በኤች.አይ.ቪ. የተያዙ ሆነው ተገኝተዋል።
- እድሜያቸው ከ10 እስከ 24 ከሆኑት ታዳጊ ወጣቶች መካከል የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭት የሴቶቹ ከወንዶቹ በሦስት እጥፍ የሚበልጥ ሲሆን በዚህም መሰረት የሴቶቹ 0.3 በመቶ ሲሆን የወንዶቹ 0.1 በመቶ ነው።

የመጨረሻውን መረጃ እንኳ ብንወስድ በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ በሦስት እጥፍ እንደሚያዙ ነው። አጠቃላይ የሀገሪቱ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭት ከ1.3 በመቶ በላይ ደርሷል ሲባልና ወረርሽኝ ደረጃ ደርሷል ሲባል ችግሩ የጸናው ሴቶች ላይ መሆኑን ልብ ይሏል።

ስለዚህ ይህ ዳግም ያገረሸውን ችግር ለመቋቋም በሚደረገው ሁል አቀፍ ጥረት ውስጥ ይበልጥ ለችግሩ ተጋላጭ ለሆኑት ሴቶች የተለየ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ የችግሩ ስፋትና ጥልቀት ያስገድደናል።

ከድንገተኛ ሞት ይሰውረን

<<ከድንገተኛ ሞት ይሰውረን>> የሚለው አባባል በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ የዘወትር ምኞት ነው። ግን ደግሞ ድንገተኛ ሞት ሁሌም ይከሰታል። የምናውቀው ሰው በድንገት ሞተ ተብሎ ሲነገረን እገሌ ታሞ ሞተ ከሚለው የበለጠ ያስደነግጣል። << ምነው ትናንት አይቼው? ይሄ ፍጹም አይታመንም>> እንላለን። ድንገተኛ ሞትን ሁሌም ለማመን እንቸገራለን።

ግን ድንገተኛ ሞት እንዴት ይከሰታል? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት የህክምናውን ዘርፍ ደጃፍ ማንኳኳት የግድ ይለናል። ሰሞኑን አንድ ታዋቂ የጤና ድረ ገጽ በድንገተኛ ሞት ጉዳይ ያወጣው መረጃ እጅግ ተቃሚ ሆኖ ስላገኘነው ልናካፍላችሁ ወደድን።

በመረጃው መሰረት በርካታ ሰዎች ለድንገተኛ ሞት የሚዳረጉት ማታ በድንገት ከእንቅልፋቸው ነቅተው ወደ መጸዳጃ ቤት ሲሄዱ ወይም ውሀ ጠምቷቸው ለመጠጣት ሲንቀሳቀሱ ነው። ሰዎች በድንገት ከእንቅልፋቸው ብድግ ብለው ሲንቀሳቀሱ ተዝለፍልፈው ይወድቁና በዛው እስከወዲያኛው ያሸልባሉ።

በዘርፉ ጥልቅ ምርምር ያደረጉ የጤና ባለሙያዎች እንደሚያስረዱት ማንኛውም ሰው በሚተኛበት ሰዓት ልቡም በከፊል እረፍት ላይ ይሆናል። በእንቅልፍ ሰዓት ልብ ሙሉ በሙሉ እረፍት ላይ ባይሆንም ንቁ በሆነበት ጊዜ እንደሚያከናውነው ሁሉ ለሰውነታችን የሚያስፈልገውን ደም ለሁሉም የሰውነታችን ክፍል አይሰጥም።

ስለዚህም አንድ ሰው በድንገት ከእንቅልፉ ተነስቶ ሲንቀሳቀስ እንደ አንጎል ያሉ የሰውነት ክፍሎች በቂ ደም አያገኙም። አንጎል በቂ ደም ካላገኘ ደግሞ የሰውነት የተለያዩ ክፍሎችን መቆጣጠር አይችልም። በዚህ መሀል እራስን መሳትና ተዝለፍልፎ መውደቅ ሊከሰት ይችላል። ይህ ሁኔታ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ድንገተኛ ሞት ሊያስከትል ይችላል።

በተለይ ቀድሞውኑ የተለያዩ የጤና እክል ያለባቸው ከሆኑ፣ ከፍተኛ የአልኮል መጠጥ ጠጥተው ከሆነና በእድሜ የገፉ አዛውንት ከሆኑ በድንገት ከእንቅልፍ ተነስቶ መንቀሳቀስ አደጋውን ያባብሰዋል።

እና መፍትሄው ምንድነው? ሰዎች ከድንገተኛ ሞት ራሳቸውን ለመጠበቅ ምን ማድረግ አለባቸው? ተመራማሪዎቹ ምክር አላቸው። አንድ ሰው በድንገት ከእንቅልፉ ተነስቶ ከመንቀሳቀሱ በፊት የሚከተሉትን ጥንቃቄዎችን እንዲያደርግ ባለሙያዎቹ ይመክራሉ።

1ኛ. *አንድ ሰው ከእንቅልፉ እንደነቃ ለአንድ ደቂቃ ያህል አልጋው ላይ በተኛበት ሁኔታ መቆየት አለበት*

2ኛ. *ቀጥሎ አልጋው ላይ እግሩን ሳያወርድ መቀመጥ። በዚህ ሁኔታ ከአልጋው ሳይወርድ ለአንድ ደቂቃ ያህል መቀመጥ*

3ኛ. *በመጨረሻም እግሩን ከአልጋው ላይ አውርዶ ወለሉን በመርገጥ አልጋው ላይ ለሶስት ደቂቃ ያህል መቀመጥ*

ይህ የአምስት ደቂቃ ያህል ጊዜ ከእንቅልፋችን ሙሉ በሙሉ እንድንነቃና በከፊል ዕረፍት ላይ የነበረው ልባችን ለሁሉም የሰውነት ክፍሎቻችን በበቂ ሁኔታ ደም እንዲያሰራጭ በቂ ጊዜ ይሰጠዋል። ከዚህ በኋላ ሌላ ጽኑ የጤና ችግር ከሌለ በስተቀር ተነስተን ስንንቀሳቀስ እራስን መሳትና ተዝለፍልፎ የመውደቅ አደጋ በእጅጉ ይቀንሳል። እናም ከእንቅልፍ በድንገት ተነስቶ በመንቀሳቀስ የሚከሰተውን ድንገተኛ ሞት ከላይ የተጠቀሱትን ጥንቃቄዎች ተግባራዊ በማድረግ በእጅጉ መቀነስ እንደምንችል የጤና ባለሙያዎቹ ይመክራሉ።

ከኮሮና ቫይረስ እራሳችንንና ወገናችንን እንጠብቅ

Initiative Africa

የፊት ጭምብል መጠቀም

በየቤታችን መቀመጥ

እጅን በአግባቡ መታጠብ
እና ማፅዳት

ይህ የሚደገፈው፡
EMBASSY OF SWEDEN
Addis Ababa

ቦሌ መድሃኒአለም ከኤድና ሞል ጀርባ
ላኪ ፎቅ 5ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 505
ስልክ ቁ፡ 011 662 26 40/ 41
ፋክስ ቁ፡ 011 662 26 42 | ፖ ሳ ቁ፡ 1123
ኢሜል፡ info@initiativeafrica.net
ድ ገፅ፡ www.initiativeafrica.net